# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 031 ጥቅምት 1 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ‹‹ታማኝ ግብር ከፋዮች የኢትዮጵያን ክብር የሚያስጠብቁ ናቸው››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



ጌትነት ምሕረቴ

አዲስ አበባ፡- ታማኝ ግብር ከፋዮች የኢትዮጵያን ክብር የሚያስጠብቁና ብልፅግና እንዲረጋገጥ የሚተጉ ናቸው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) 6ኛ ዙር የታማኝ ግብር ከፋዮች የምስጋናና የዕውቅና ሽልማት መርሐ ግብር ትናንት በአንድነት ፓርክ ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ግብር መክፈል ለታማኝ ግብር ከፋዮች ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ አሻራ ማኖር ነው። ታማኝ ግብር ከፋዮች የኢትዮጵያን ክብር የሚያስጠብቁና ብልፅግና እንዲረጋገጥ የሚተጉ ናቸው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ብልፅግና የሚረጋገጠው በኢትዮጵያውያን ብቻ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብልፅግናን ለማረጋገጥና የሀገር ክብር ለማስጠበቅ የሚቻለው በታማኝነት ግብር በመክፈል እንደሆነ ተናግረዋል።

በታማኝ ግብር ከፋዮች ልክ መንግሥትም እንደሚታመን አመልክተው፤ ከግብር የተገኘውን ገቢ በዓይን በሚታዩና በእጅ በሚጨበጡ የልማት ሥራዎች ላይ በማዋል በከተሞች፣ በገብርና እና በመሠረተ ልማት

‹‹ታማኝ ግብር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከሊባኖስ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የመመለስ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል

ሞገስ ፀጋዬ

አዲስ አበባ፡- በሊባኖስ በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የመመለስ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነብያት ጌታቸው እንደገለጹት፣ በሊባኖስ የተፈጠረውን ቀውስ ተከትሎ የዜጐች ደኅንነት ችግር ላይ እንዳይወድቅ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው።

በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ሀገራት በዜጎች ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ተከትሎ ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎችን ልዩ ትኩረት በመስጠት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ጥረት እየተደረገ ነው

ከሊባኖስ ለችግር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ታደሰ ኩማ (ዶ/ር)

## በቴክኖሎጂ መታገዝ የሚያስፈልገው የአየር ንብረት ለውጥ

ሔርሞን ፍቃዱ

የአየር ንብረት ለውጥ ዓለምን በእኩል ሁኔታ የሚጎዳ እና ለመቆጣጠር የሚያዳግት ክስተት ነው። በተለይ ለአፍሪካ እና ለሀገራችን እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ከሆነ ውሎ አድሯል። ይህንን ጉዳት ለመከላከል እና ለመቅረፍ በየጊዜው ጥናቶች እየተጠኑ በፖሊሲ እና በአሠራር በመንግሥት ተግባራዊ ይደረጋሉ።

በቴክኖሎጂ መታገዝ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከ801 ሺህ በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ እየሆኑ ነው

- 16 ሺህ እናቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ በዘንድሮው ዓመት ከ801 ሺህ በላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኙ ተገለጸ። በዚህም 16 ሺህ የሚሆኑ እናቶች የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸው ተጠቁሟል።

6ኛው "የሚላን የከተማ የምግብ ፖሊሲ ስምምነት" ፎረም በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ጃንጥራር አባይ በመድረኩ ባደረጉት ንግግር፣ ጤናማ እና ፍትሐዊ ዓለምን ለመገንባት የተቀናጀ ስትራቴጂ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ለዚህ ደግሞ የትምህርት ቤት የምግብ ፕሮግራሞች ላይ ኢንቨስት ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል። በዚህ ረገድ አዲስ አበባ የተሻለ ተሞክሮ እንዳላት ጠቁመዋል።

በከተማዋ በዘንድሮው ዓመት ከ801 ሺህ በላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ መሆናቸውንና 16 ሺህ የሚሆኑ እናቶች የሥራ ዕድል እንዳገኙ አስታውቀዋል።

ከ801 ሺህ በላይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# "ውትድርና ለሀገር ሉዓላዊነት መስዋዕትነት የሚከፈልበትና ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪክ የሚጻፍበት ዘርፍ ነው"

- ሌተናል ጄኔራል አብዱራሃማን እስማኤል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ጦላይ፡- ውትድርና ለሀገር ሉዓላዊነት፤ ለሕዝቦች ሁለንተናዊ ዕድገት መስዋዕትነት የሚከፈልበት እንዲሁም በጀግንነት ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪክ የሚጻፍበት የሙያ ዘርፍ ነው ሲሉ በመከላከያ ሚኒስቴር የሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጄኔራል አብዱራሃማን እስማኤል ገለጹ።

የጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግተኛ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት በመሠረታዊ ውትድርና ሥልጠና ያሠለጠናቸውን መሠረታዊ ወታደሮች ትናንት አስመርቋል።

ውትድርና ከሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ጉዞ ጋር እያደገ የመጣ ለሀገር ሉዓላዊነትና ለሕዝብ ሠላም ሲባል እራስን አሳልፎ የሚሰጥበትና ለትውልድ የሚተላለፍ የጀግንነት ታሪክ የሚጻፍበትም መሆኑን ሌተናል ጄኔራል አብዱራሃማን በዕለቱ ገልጸዋል።

ሌተናል ጄኔራል አብዱራሃማን አክለውም፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ በፅናትና በጀግንነት ግዳጁን በብቃት እየፈጸመ ይገኛል ያሉ ሲሆን፤ ሠራዊቱ በየጊዜው ለሚፈጠሩ ችግሮች ሳይንበረከክ ሕዝቡንና ሀገሩን በፍትሐዊነት እያገለገለ ነው ብለዋል።





ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ ፈታሞ ዱባለ

የኢትዮጵያ ጀግኖች ልጆቿ አይበገሬነት ለረጅም ዓመታት ሀገርን ከጠላት ተከላክሎና ጠብቆ የማቆየት ታሪክ በዛሬው ትውልድም እየተደገመ የሚገኝ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ሌተናል ጄኔራል አብዱራሃማን ገለጻ፤ ሀገሪቱ ሁለንተናዊ ብቃቱን ያረጋገጠ መከላከያ ሠራዊት እየገነባች ትገኛለች። ተመራቂዎች ወደ ተመደቡበት ቦታ በመሄድ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር ግዳጅ ሲቀበሉ በእያንዳንዱ ተልዕኮ ጀርባ የኢትዮጵያ ፍቅርና ክብር እንዲሁም ሉዓላዊነቷ ማስቀደም አለባቸው።

ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት ኢትዮጵያን ከውጭ ታሪካዊ ጠላቶቿ በመከላከል የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል ሉዓላዊነቷ ሳይደፈር አቆይቷል ያሉት ሌተናል ጄኔራል አብዱራሃማን፤ ተመራቂዎች በገቡት ቃል መሠረት በትጋትና በፍትሐዊነት ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ አሳስበዋል።

የጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግተኛ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ዋና አዛዥ ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ ፈታሞ ዱባለ በበኩላቸው፤ ሀገርን ከተለያዩ ጥቃቶች ለመከላከል የወታደራዊ ሳይንስ ማወቅና ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ነው።

ተመራቂዎቹ ለዘጠነኛ ዙር የመሠረታዊ ውትድርና ሥልጠና ሲከታተሉ የነበሩ ሠልጣኞች መሆናቸውን ተናግረዋል።

ትምህርት ቤቱ ከአመለካከት ጀምሮ ሁለገብ የሆነ ሥልጠና በመስጠት ለሀገር ሉዓላዊነት የሚተጉ የሠራዊት አባላት እያፈራ ይገኛልም ነው ያሉት።

ወታደር እውቅ፣ ብቁና የታጠቀ ነው ያሉት ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ ፈታሞ ዱባለ፤ በውስጥና በውጭ የኢትዮጵያን ጠላቶች ለመመከትና ሉዓላዊነቷን ለማስጠበቅ የሚዋደቅ ነውም ብለዋል።

ሠልጣኞቹ በመሠረታዊ ውትድርና ማግኘት ያለባቸውን የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ሥልጠናዎችን በተገቢው መንገድ ማግኘታቸውን ገልጸዋል።

## ለአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ትግበራ መሳካት ቻይና ድጋፏን አጠናክራ ትቀጥላለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ለአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ትግበራ መሳካት ቻይና ድጋፏን አጠናክራ እንደምትቀጥል በአፍሪካ ኅብረት የቻይና ተወካይ አምባሳደር ሁ ቻንግቹን ገለጹ።

የዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ኢንሼቲቭ ሙሉ ትግበራና የቻይና አፍሪካ የልማት ትብብር ተጠናክሮ በሚቀጥልበት ሁኔታ ላይ በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት ውይይት ተካሂዷል።

በአፍሪካ ኅብረት የቻይና ተወካይ አምባሳደር ሁ ቻንግቹን፤ ቻይና ከአፍሪካ ጋር ያላትን ሁለንተናዊ የልማት ትብብር አጠናክራ መቀጠሏን አንስተዋል።

ዓለም አቀፍ የልማት ትብብሮችን በጋራ ተጠቃሚነት መርሕ በትብብር መተግበር፣ የቻይና አፍሪካ የተባበሩት መንግሥታት የትብብር ልኅቀት ማዕከል እንዲቋቋም መሥራት ከቀጣይ ትኩረቶች መካከል መሆናቸውንም ተናግረዋል። በንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ጤና፣ ግብርና፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ የአረንጓዴ ልማትና የፀጥታ መስኮች ላይም እንዲሁ።

ለአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ትግበራ መሳካት ቻይና ድጋፏን አጠናክራ የምትቀጥል መሆኑንም አምባሳደሩ አረጋግጠዋል።

ለረጅም ዘመናት የተሻገረው የአፍሪካ ቻይና ትብብር ለደቡብ ደቡብ ትብብር ምሳሌ እንደሆነ የገለጹት ደግሞ በአፍሪካ ኅብረት የትምህርት፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መሐመድ ቤልሆሲኒ ናቸው።

የዘላቂ ልማት ግቦችና አጀንዳ 2063 እውን በማድረግ የተሻለች ዓለምን ለአሁኑና ለቀጣይ ትውልድ ለመፍጠር ቻይና ከአፍሪካ ጋር ያላትን ትብብር የበለጠ ታጠናክራለች ብለዋል።

የቻይና ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ኤጀንሲ ምክትል ሊቀመንበር ዛኦ ፈንግታኦ፤ የቻይና አፍሪካ ትብብር በተለያዩ ዘርፎች ተጨባጭ ለውጥ ማምጣቱን ገልጸዋል።

ቻይና ዓለም አቀፍ የልማት ትብብርና በደቡብ ደቡብ ትብብር ፈንድ በማቅረብ፣ በሥልጠና እና ሌሎች የልማት ትብብር ዘርፎች እያደረገች ያለውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥልም አረጋግጠዋል።

የዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ኢንሼቲቭ የ2030 ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት እንደሚያግዝ ጠቅሰው እስካሁን 30 የአፍሪካ ሀገራት በይፋ መቀላቀላቸውን አክለዋል።

ቻይና ለዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ኢንሼቲቭ ሙሉ ትግበራ እና የቻይና አፍሪካ የልማት ትብብርን የበለጠ ለማጠናከር ዝግጁ መሆኗንም አረጋግጠዋል።

የአፍሪካ ሀገራት ለሚተገብሯቸው የልማት ስትራቴጂዎች ቅድሚያ በሚሰጣቸው የልማት ዘርፎች ድጋፍ በማድረግ ትብብሩ እንደሚቀጥልም እንዲሁ።

በውይይቱ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት ተወካዮች፣ አምባሳደሮችና ሌሎች የተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል ሲል የዘገበው ኢዜአ ነው።



## የኤሌክትሮኒክስ ፊርማን ጨምሮ ሌሎች ረቂቅ አዋጆች ለዝርዝር ዕይታ ለቋሚ ኮሚቴዎች ተመሩ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኤሌክትሮኒክስ ፊርማን ጨምሮ ሌሎች አምስት ረቂቅ አዋጆችን ለዝርዝር ዕይታ ለቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በትናንትናው ዕለት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ስብሰባውን አካሂዷል።

ምክር ቤቱ ባካሄደው ስብሰባ ስድስት ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል።

ምክር ቤቱ የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ፣ የኢትዮጵያ የሕንፃ፣ የእንስሳት ጤና እና ደኅንነት፣ የመድኃኒት ፈንድና የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ማቋቋሚያ፣ ጤና አገልግሎት አስተዳደር እና ቁጥጥር፣ የሪል ስቴት ልማት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ ለዝርዝር ዕይታ ነው ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች የመራው።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ መሠረት ኃይሌ የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ማሻሻያ አዋጅ ሕጋዊ ዕውቅና ለመስጠት እና በዲጂታል የፊርማ ሥርዓት ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ሚና መብት እና ግዴታ ለመደንገግ የረቂቅ አዋጁ መሻሻል አስፈላጊ መሆኑን ለምክር ቤቱ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ በዲጂታል ኢኮኖሚው ያላትን ዝግጁነት ለማረጋገጥ እና በዘርፉ መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም ረቂቅ አዋጁ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል።

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው የሚመራለት ቋሚ ኮሚቴ የረቂቅ አዋጁን መሻሻል ያለውን ዘርፈ ብዙ ጥቅምና ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት በጥልቀት ሊያየው እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ የሕንፃ ረቂቅ አዋጅ የአገልግሎት ለውጥ ሥራ የሕዝብን ጤንነትና ደኅንነት ለመጠበቅ እና የሕንጻ ተደራሽነትን ለአካል ጉዳተኞችና ለማኅበረሰቡ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ሚኒስትር ዴኤታዋ አመልክተዋል።

እያጋጠሙ ላሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፤ የግንባታ ጥራት እና የሃብት ብክነት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ግልፅና ምቹ የሆነ የአሠራር ሥርዓትን ለመዘርጋት ረቂቅ አዋጁ አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል።

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው፤ በከተሞች የሚገነቡ ሕንፃዎች የመሬት የመሸከም አቅም፤ የአካል ጉዳተኞችን ደኅንነት እና የአካባቢን ተፅዕኖ ታሳቢ ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

የእንስሳት ጤና እና ደኅንነት ረቂቅ አዋጅ በእንስሳት ሃብት ልማት የሕዝቡን ተጠቃሚነትና በዘርፉ ዓለም አቀፍ የገበያ ተወዳዳሪነትን ለመፍጠር እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የእንስሳት ተዋፅዖ ምርትን ለማሳደግ እና ለማሻሻል ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ መሠረት ገልጸዋል።

ዜጎች በእንስሳት ሃብት ልማት ተጠቃሚ እና ጤናማ የኑሮ ዘይቤ ለመፍጠር ያስችል ዘንድ በሕግ ማዕቀፍ ማካተቱ ተገቢ መሆኑንም ገልጸዋል።

ምክር ቤቱም የቀረበለትን ረቂቅ አዋጅ ለዝርዝር እይታ ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምፅ መርቷል።

በተመሳሳይ ምክር ቤቱ፤ የመድኃኒት ፈንድና የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎትን ለማቋቋም የቀረበ ረቂቅ አዋጅን እና የጤና አገልግሎት አስተዳደርና ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ መርምሮ ለዝርዝር እይታ ለጤና፤ ማኅበራዊ ልማት፤ ባሕልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምፅ መርቷል።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ የሪል ስቴት ልማት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ የቀረበለትን ረቂቅ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 6/2017 አድርጎ ለዝርዝር እይታ ለከተማ፣ መሠረተ-ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምፅ መርቷል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ ባደረገው ስብሰባ የምክር ቤቱን 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 1ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መርምሮ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል።

# ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ጥቅምት 4 በሀገር አቀፍ ደረጃ በድምቀት ይከበራል

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ በድምቀት እንደሚከበር የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስታወቀ።

ምክር ቤቱ ለኢፕድ በላከው መግለጫ፤ የብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በየዓመቱ እየተከበረ አስራ ስድስት ዓመታትን አስቆጥሯል። በያዝነው ዓመትም “ሰንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ከፍታ” በሚል መሪ ሃሳብ ለ17ኛ ጊዜ በመላ ሀገሪቱ ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

ስለሆነም የፊታችን ሰኞ ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም በፌዴራል፣ በክልሎችና በሁለቱም የከተማ አስተዳደር ከተሞች ከሰንደቅ ዓላማ መርሆዎች ጋር ተገናዝቦ በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሪነት በመላው ሀገሪቱ እንደሚከበር ተገልጿል።

ሰንደቅ ዓላማ የመስዋዕትነት፣ የነፃነት፣ የሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ዓርማ ምልክት ነው ያለው በመግለጫው፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰንደቅ ዓላማ ትልቅ ስፍራና ትርጉም ያለው ነው ሲል አትቷል።

ሰንደቅ ዓላማ በልባችን የታተመ የአንድነታችን፣ የሉዓላዊነታችንና የነፃነታችንን መገለጫ ታላቅ ሀገራዊ ዕሴት በማለት፤ የአብሮነታችን ዓርማ ምልክት ነው ብሏል።

የሀገር ዳር ድንበርን ጥሶ ነፃነታችንንና ሉዓላዊነታችንን ለመውሰድ በየዘመናቱ በተደጋጋሚ የመጣን የውጭ ወራሪ የጠላት ኃይልን እናት አባቶቻችን በተባበረ ክንድ በአንድነት ቆመው መክተውና አሳፍረው የመለሱት ለሀገርና ለሰንደቅ ዓላማ ከሚሰጡት ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት በመነሳት ነው ሲልም አክሏል።

ስለሆነም ሰንደቅ ዓላማችን ተገቢውን ክብርና ገናና ከፍታውን ይዞ ከትውልድ ትውልድ ተላልፎ እነሆ ከአሁኑ ትውልድ ደርሷል ብሎም፤ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ለሰንደቅ ዓላማ ተገቢውን ክብር መስጠትና ተገቢውን ክብር እንዲያገኝ ማድረግ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነትና ታሪካዊ አደራም ጭምር ነው ሲል ገልጿል።

የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን በዓል በየዓመቱ መከበሩ ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ከፍታ ቀጣይነት ብሔራዊ መነቃቃትን ለመፍጠር ትልቅ ትርጉም የሚኖረው መሆኑን በመጠቆም፤ ለሀገርና ለሰንደቅ ዓላማ ያለንን እውነተኛ ክብርና ፍቅር ሁላችንም እንደዜጋ የምንገልፅበትና ለዚህም በሰንደቅ ዓላማ ፊት ዳግም ቃላችንን የምናድስበት ዕለት ይሆናል ብሏል መግለጫው።

በዕለቱ በፌደራል የመንግሥት ተቋማት፣ በክልሎችና በሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች፣ በመከላከያ ሠራዊት ካምፖች እንዲሁም በየኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ሚሲዮኖች በተመሳሳይ ሰዓት ከረፋዱ 4፡30 ሰዓት ላይ ሰንደቅ ዓላማ በመስቀልና በሰንደቅ ዓላማ ፊት ቃለ መሐላ በመፈፀም ሥነ-ሥርዓት እንዲሁም በተለያዩ ዝግጅቶች በደማቅ ሁኔታ የሚከበር ይሆናል።

# ለዘላቂ ሠላም መስፈን የድርሻቸውን እንደሚወጡ በምዕራብ ጎንደር ዞን የሃይማኖት አባቶች ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በአካባቢያቸው ፍቅርና አንድነትን በመስበክ ለዘላቂ ሠላም መስፈን አበክረው በመሥራት የድርሻቸውን እንደሚወጡ በምዕራብ ጎንደር ዞን የሃይማኖት አባቶች ገለጹ።

በዞኑ ገንዳ ውኃ ከተማ በሠላም ዙሪያ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች የተሳተፉበት የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

ከመድረኩ ተሳታፊዎች መካከል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምዕራብ ጎንደር ዞን ሀገረ ስብከት የሰንበት ትምህርት ቤቶች መምሪያ ኃላፊ ሊቀ ሥዩማን ገብረሥላሴ ገብረማርያም፤ የሠላም ዕሴቶችን መጠበቅ ለዘላቂ ሠላም መስፈን ዓይነተኛ ሚና እንዳላቸው ተናግረዋል።

ቤተክርስቲያን ፍቅርና አንድነትን በመስበክ ጥላቻና ግጭትን እንደምታወግዝ ጠቅሰው፤ ለሕዝበ ክርስቲያኑ አስፈላጊውን ትምህርት በመስጠት ለፍቅርና ሠላም መስፈን እንደሚሠሩ አረጋግጠዋል።

ሠላም ለሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ሕይወት ላለው ፍጡር ሁሉ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አንስተው፤ የሠላም ባለቤት የሰው ልጅ በመሆኑ ሠላሙን ማስጠበቅ እንዳለበት ተናግረዋል።

የገንዳ ውሃ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሼህ አሕመድ ኑርዬ በበኩላቸው፤ ሠላም እንዲሰፍን ማድረግ የሃይማኖት አባቶች ኃላፊነት ጭምር መሆኑን ገልጸዋል።

ሃይማኖቶች ሠላምን መሻትና ለሠላም መሥራት እንደሚያስተምሩም አመልክተዋል።

ተጠብቀው የቆዩ የአንድነትና የአብሮነት እሴቶችን ማስቀጠል እንደሚገባ አመልክተው፤ ሕዝበ ሙስሊሙ ከሌሎች የእምነቱ ተከታዮች ጋር በመሆን ለዞኑ ብሎም ለሀገር ግንባታና ሠላም መሥራት እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ሌላኛው የመድረኩ ተሳታፊ የሀገር ሽማግሌ አቶ ሲሳይ ይመር በበኩላቸው፤ ለሠላም ዘብ መቆም የፀጥታ አካሉ ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ግለሰብ ኃላፊነት መሆኑን ተናግረዋል።


ትውልዱ የሠላምን እሴቶችን እንዲጠብቅ የሃይማኖት አባቶች አስተምህሮ ትልቅ ድርሻ እንዳለው የተናገሩት ደግሞ በሀገር መከላከያ ሠራዊት የሰሜን ምዕራብ ዕዝ የ504ኛ ኮር አስተባባሪ ብርጋዴል ጄኔራል አብደላ ሙሐመድ ናቸው።

ትውልዱ ለዘላቂ ሠላም መስፈን በላቀ ትብብር መሥራት እንደሚገባውም አብራርተዋል።

የምዕራብ ጎንደር ዞን ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ አንዳርጌ ጌጡ በበኩላቸው፤ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ችግር በሠላም እንዲፈታ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ሕግን ማክበርና ለሕግ ተገዥ መሆን የሀገሪቱ እሴቶች መሆናቸውን ለወጣቱ ትውልድ ማስተማር ያለባቸው መሆኑንም ተናግረዋል።

በምክክር መድረኩ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል።



አቶ አካሉ ሐልቻዬ

# በጌዴኦ ዞን እያንዳንዱ ዜጋ የሥራ ዕድል እንዲያገኝ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በትኩረት እየሠሩ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ዲላ፡- በጌዴኦ ዞን እያንዳንዱ ዜጋ የሥራ ዕድል እንዲያገኝ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በትኩረት እየሠሩ መሆኑን የዞኑ ቴክኒክና ሙያ መምሪያ አስታወቀ።

የጌዴኦ ዞን ቴክኒክና ሙያ መምሪያ ኃላፊ አቶ አካሉ ሐልቻዬ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በጌዴኦ ዞን አራት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት አሉ። እነዚህም በሁለት ዘርፍ ተማሪዎችን ተቀብለው ሙያዊ ሥልጠናና የቴክኒክ እውቀት እየሰጡ ይገኛል። ተቋማቱ የመደበኛ የቴክኒክና የሙያ ሥልጠና እና አጫጭር ሥልጠናዎች ይሰጣሉ።

የጌዴኦ ዞን ነዋሪዎችን ቢያንስ የአንድ ሙያ ባለቤት በማድረግ እያንዳንዱ ዜጋ የሥራ ዕድል እንዲያገኝ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በትኩረት እየሠሩ ነው ያሉት አቶ አካሉ ሐልቻዬ፤ ለዚህም በዞኑ 12ተኛ ክፍል የጨረሱ ተማሪዎችን በፍላጎታቸው መሠረት ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎች እየተመቻቹ መሆኑን ገልጸዋል።

በ2016 ዓመተ ምሕረት ማኅበረሰቡ ለቴክኒክና ሙያ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን፣ የመሠረተ ልማት መጓደል እንደነበር አንስተው፤ በተጨማሪም የሙብራት፣ የውሃና ሌሎች መሰል ጉዳዮች፣ የማሠልጠኛ ማሽኖች እጥረት፣ ዘመኑን የዋጁ ማሽኖች በኮሌጆቹ አለመኖር ተጠቃሽ ተግዳሮቶች እንደነበሩ ተናግረዋል።

መንግሥት በክህሎት መር ሥልጠና ላይ ትኩረት እያደረገ ነው። ይህን ተከትሎ በዞኑ ቴክኒክና ሙያ ላይ የሚስተዋለውን ተግዳሮቶችን ለመሙላት ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት መደረጉን ገልጸው፤ በ2017 ዓ.ም ተግዳሮቶቹን ወደ ውጤት ለመቀየር በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

ተቋማቱ በአልሙኒየም፣ በእንጨት፣ በብረት እንዲሁም በሌሎች ሥራዎች ላይ የቴክኒክ እና የሙያ ሥልጠናዎችን እንደሚሰጡ የገለጹት አቶ አካሉ ሐልቻዬ፤ እነዚህ ሙያዎች ገበያው በስፋት የሚፈልጋቸው ዘርፎች ናቸው። በነዚህም የዞኑ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት እየሠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህም በዘርፉ ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ለማሟላት ይረዳል ብለዋል። የሥራ አጥ ቁጥርን በመቀነስም እያንዳንዱ ዜጋ የሥራ ዕድል እንዲያገኝ ያደርጋል ያሉት አቶ አካሉ፣ ይህም የሥራ ፍቅር ያለው ትውልድ እንዲፈጠር ከማድረግ ባለፈ እንደሀገር ያለብንን ድህነትን ለመቅረፍ ይረዳል ነው ያሉት።

# ከሊባኖስ ለችግር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሠራ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ በዚህም በሊባኖስ በተከሰተው ችግር ዙሪያ በዜጎች ላይ የደረሰውን ችግር ለመታደግ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተጠቃሽ መሆናቸውን አንስተዋል።

ቀደም ሲል የተቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴ መኖሩን በመጥቀስ፤ የሊባኖስ ችግር ሲከሰት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ የቅርብ ክትትል እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በዚህም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ 51 ኢትዮጵያውያንን በዮርዳኖስና በካይሮ በኩል በተደረጉ ሁለት በረራዎች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ማድረግ መቻሉን ጠቁመው፤ ወደፊትም አጠናክሮ ለማስቀጠል ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች በቦታው በመገኘት ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት እየተሞከረ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

በሊባኖስ የሚገኘው የኢትዮጵያ የቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የምዝገባ ሥርዓት ዘርግቶ በአካልና በዲጂታል ምዝገባ እያከናወነ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ በዚህም መሠረት ከሦስት ሺህ በላይ ዜጎች ተመዝግበዋል። እንዲሁም በሊባኖስ ውስጥ አንጻራዊ ሠላም ወደ አለባቸው አካባቢዎች እንዲንቀሳቀሱ የማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሴቶችና ሕጻናት ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ሁሉንም አማራጮች ለመጠቀም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክርና ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

ችግሩ የመጣው በኢትዮጵያ ዜጎች ብቻ አይደለም ያሉት አምባሳደር ነቢያት፤ የበርካታ ሀገራት ዜጎች በሊባኖስ እንደሚኖሩ በመጠቀም በኢትዮጵያ በኩል ከመንግሥት ጥረት በተጨማሪ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ በሊባኖስ ርስ በርስ እየተረዳዳ መሆኑን ተናግረዋል። ተፈናቃዮች የሚጠለሉባቸውን ተጨማሪ ቤቶችን ተከራይተው ዜጎችን ከችግር የመታደግ ሥራ እየሠሩ እንደሚገኙም ነው የተናገሩት።

በተያያዘ ዜና አምባሳደር ነቢያት እንዳብራሩት፤ ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት አባል ሆና ተመርጣለች። በዚህ መሠረት ከ2025 አንስቶ እስከ 2027 ለሦስት ዓመት የምክር ቤት አባል ሆና ትቆያለች ብለዋል።

ይህ በኒውዮርክ በተካሄደ የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በተደረገ ድምፅ አሰጣጥ ላይ የተገኘ ውጤት መሆኑን ጠቅሰው፤ በጠቅላላ ጉባኤው ላይ 193 ሀገራት የተገኙ ሲሆን 171 ሀገራት ድጋፋቸውን በመስጠት ኢትዮጵያ አባል እንድትሆን መርጠዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት ምክር ቤት ውስጥ የፖለቲካና የሲቪል መብቶች በዓለም ላይ እንዲከበሩና ለታዳጊ ሀገራት የሚሰጡ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ሥራዎች እንዲያድጉ ትኩረት ሰጥታ ትሠራለች ሲሉ ጠቅሰዋል።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 79ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ኢትዮጵያ ውጤታማ የዲፕሎማሲ ሥራ ሠርታለች ያሉት አምባሳደር ነቢያት፤ በቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና በአሁኑ ፕሬዚዳንት አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ብሔራዊ ጥቅሞችን በሚያስከብሩ በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ አድርጓል። በዚህም የኢትዮጵያ ሚና ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ያስቻለ ሥራ ተሠርቷል ሲሉ ገልጸዋል።

# ‹‹ታማኝ ግብር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ግንባታዎች ተጨባጭ ውጤቶች መመዝገባቸውን ገልጸዋል።

ግብር መክፈል ለአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ የሀገር ግንባታ ለማካሄድ እንደሚጠቅም ጠቁመው፤ በከተሞች ሆነ ከከተሞች ውጪ መሠረተ ልማቶች የተገነቡት በታማኝ ግብር ከፋዮች በተገኘ ገንዘብ መሆኑን አውስተዋል።

ያደጉ ሀገራት እዚህ የደረሱት ጥረው ግረውና በታማኝነት ግብር ከፍለው ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ታማኝ ግብር ከፋይ ኩባንያዎች አሁን ያለው ትውልድ ለሀገር ታማኝና ታታሪ እንዲሆን ልምዳቸውን ማስተላለፍ እንደሚጠበቅባቸውም ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ግብር የመሰብሰብ መጠንና የግብር ከፋዮች ቁጥር እያደገ እንደመጣ ገልጸው፤ ይህን ገቢ ይበልጥ ለማሳደግና የሀገር ግንባታን ለማፋጠን በታማኝነት ግብር የመክፈል ባሕል እየዳበረ ሊመጣ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በመንግሥት በኩል የተጀመረውን የገቢ አሰባሰብ የአሠራር ማሻሻያን በማጠናከር፣ ሌብነትን በመቀነስና በቴክኖሎጂ የታገዘ አሠራርን በማስፋፋት ገቢ የመሰብሰብ አቅምን ለማሳደግ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

በስድስተኛው ዙር የታማኝ ግብር ከፋዮች የምስጋናና የእውቅና ሽልማት መርሐ ግብር በተለያዩ መስፈርቶች 66 ኩባንያዎች በፕላቲኒየም፣ 165 ኩባንያዎች በወርቅ፣ 319 ኩባንያዎች የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ ሲሆኑ ባለፉት አራት ዓመታት በታማኝነት ከፍተኛ ግብር በመክፈላቸው ተሸላሚ የሆኑ 20 ኩባንያዎች ደግሞ ልዩ ተሸላሚ በመሆን ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በዕለቱም በ2016 በጀት ዓመት የተሻለ የታክስ ሕግ ተገዢነት ላስመዘገቡ 550 ግብር ከፋዮች እውቅናና ምስጋና የተሰጠ ሲሆን ለሀገሪቱ የገቢ ዕድገት የእነዚህ ግብር ከፋዮች ሚና ትልቅ መሆኑም ተጠቅሷል።

በሁለቱም ተቋማት በተደረጉ ጥረቶች በ2016 በጀት ዓመት ግብር ለመሰብሰብ በእቅድ ከተያዘው 529 ቢሊዮን ብር ውስጥ 512 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ እንደተቻለ የገቢዎች ሚኒስቴር ገልጿል። ይህ አፈጻጸም በ2015 በጀት ዓመት ከነበረው 442 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ እድገት እንዳለው ታውቋል።

በተያያዘ ዜና እጅግ አስደናቂ የሆነውን አንድ ሚሊዮን ቶን ቡና የማምረት ግባችንን አሳክተናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ገልጸዋል።

“ቡናችን ለብልፅግናችን” በሚል መሪ ሀሳብ ትናንት በተካሄደው ሀገራዊ የቡና ኤግዚቢሽንና የዕውቅና መድረክ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቡና ምርት ላይ ለተሠማሩ ውጤታማ አርሶ አደሮች፣ አልሚዎች፣ ቡና ላኪ ማኅበራት እና ባለሀብቶች ዕውቅናና ሽልማት ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው እጅግ አስደናቂ የሆነውን አንድ ሚሊዮን ቶን ቡና የማምረት ግባችንን መተናል ብለዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ለቡና ምርትና ጥራት መጨመር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራቱንም አያይዘው ገልጸዋል።

በዚህም የኢትዮጵያ ዓመታዊ የቡና ምርትን ከአምስት ዓመታት በፊት ከነበረነት 500 ሺህ ቶን ወደ አንድ ሚሊዮን ቶን ማሳደግ መቻሉን አብራርተዋል።

ከገቢ አንጻርም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ኢትዮጵያ ከቡና ወጪ ንግድ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቷን አንስተው፤ በተያዘው በጀት ዓመት ይህን አኃዝ ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ከፍ ለማድረግ እንደሚሠራ አብራርተዋል።

ባለፉት ስድስት ዓመታት ለእድገቱ ያለንን ቁርጠኝነት በሚያሳይ ሁኔታ ስምንት ነጥብ አምስት ቢሊዮን የቡና ችግኞችን ተክለናል ሲሉ ጨምረው ገልጸዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ለቡና የእሴት ሰንሰለት የተሳለጠ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ወሳኝ ሲሆን፤ በቡና እሴት የመጨመር ተግባር ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫ ነው።

በዘርፉ የተሰማሩ ሁሉ ይህን ቁልፍ ኢንዱስትሪ የበለጠ ለማሳደግ የየድርሻቸውን እንዲወጡም ጠይቀዋል።

የሀገር ውስጥ የቡና ተጠቃሚነትም ትርጉም ባለው መልክ እድገት አሳይቷል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከተግዳሮቶቻችን ባሻገር በቡና ልማት ዘርፍ የበለጠ ስኬታማ መሆናችንን ቀጥለናል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን የዓለም ከፍተኛ ቡና አምራች ሀገራት አንዷ ለማድረግ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል።

ይህን እውን ለማድረግ ደግሞ ከመንግሥት በተጨማሪ ላኪዎች የቡና ምርት ጥራትን ለሚያሻሽሉ ተግባራት ኢንቨስት ማድረግ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

ላኪዎች ቡና ምርት ላይ ውበት ባለው አስተሻሸግ ዘዴ እሴት ጨምሮ ለወጪ ገበያ ማቅረብ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸውም ገልጸዋል።

በቡና ምርት ከብራዚል እና ቬትናም ቀጥላ በዓለም 3ኛ የሆነችውን ኢትዮጵያን ከቬትናም ጋር እኩል ለማድረግ ምርት ማሳደግ ላይ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባም አበክረዋል።

በሌላ በኩል የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ኢትዮጵያ በሁሉም መስክ በዓለም ገበያ ይበልጥ እንድትሳተፍ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

ማሻሻያውን ተከትሎ ባለፉት ሁለት ወራት ከቡና ወጪ ንግድ ከቀደሙት ዓመታት ከፍተኛ ብልጫ ያለው ገቢ መገኘቱንም አመላክተዋል።

በቀጣይም የሚገጥሙን ፈተናዎች ሳያቆሙን በሁሉም መስክ የኢትዮጵያን ብልፅግና እውን ለማድረግ እንሠራለን ሲሉ አፅንዖት ሰጥተው ተናግረዋል።

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሀገሪቱ የስፔሻሊቲ ቡናን 60 በመቶ ማድረስ መቻሏን እንዲሁም ኢትዮጵያ በዓለም ገበያ አንድ ኪሎ ግራም ቡናን በ103 ሺህ ብር መሸጥ መቻሏን አንስተዋል።

በግብይት ሠንሠለቱ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ የቡና ምርትን ለማሳደግ እና የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ይበልጥ ለማረጋገጥ እንደሚሠራም አመላክተዋል።

# በቴክኖሎጂ መታገዝ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናት ማዕከል ዳይሬክተር ታደሰ ኩማ (ዶ/ር) በኢንስቲትዩቱ የሚጠኑ ጥናቶች ዓላማቸው መንግሥት የሚሠራውን የአየር ንብረት ለውጥ ሥራ መረጃ ላይ በመመሥረት ፖሊሲዎች እና አሠራሮች እንዲዘረጉ ማድረግ መሆኑን ይጠቅሳሉ። የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ደግሞ ነባር አሠራሮችን መተካት በቴክኖሎጂ የታገዘ አሠራር እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ በተደረገው ጥናት መሠረት የማይደርቁ ተክሎች ተብለው የተቀመጡ አዝርዕቶች በከፍተኛ ሙቀት ምክንያት አፈር እና ውሃ መቋጠር ባለመቻል እየደረቁ መሆናቸውን ይጠቁማሉ ብለው፤ ለአብነትም የቡና ተክልን ያነሳሉ። በመሆኑም አምራቾች የቡና ምርትን ትተው ወደ ሌላ ምርት እንዲዛወሩ የሚያደርግ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ይገልፃሉ።

የመንግሥት ፕሮጀክቶች ተብለው ከተቀመጡት ውስጥ የግብርና ዕድገት ፕሮግራም፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም፣ የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች እና ሌሎች ኢንቨስትመንቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህን ለማሳካት ደግሞ በአየር ንብረት ዙሪያ በነባርነት የቆዩትን አሠራሮች በቴክኖሎጂ በታገዘ መንገድ መቀየር እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

አርሶ አደሩ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ድርቅ ሲያጋጥመው ያለው አማራጭ ንብረቱን ሸጦ እራሱን ማዳን መሆኑን በመጥቀስ፤ ነገር ግን የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ሴፍቲኔት በመኖሩ ቢያንስ ሀብታቸውን አቆይተው እንዲያገግሙ እንደሚያደርጋቸው ያብራራሉ።

በመሆኑም በተለይ የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል ያሉት ታደሰ (ዶ/ር)፤ ኢንቨስትመንቱ በቴክኖሎጂ የታገዘ የተፋሰስ ልማት፣ በቂ የግብርና መሠረተ ልማት መዘርጋት እንዲሁም ገበያ ትስስር ላይ ማተኮር እንዳለበት ያመለክታሉ።

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ተመራማሪ የሆኑት ጫሊ ይተፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም ከእርሻ ጋር ተያይዞ አሁን ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቅረፍ ማኅበረሰብን ያማከለ ግብርና እንዲኖር ማድረግ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አረንጓዴ ዐሻራ ለመተግበር የፖሊሲ ጥናቶች ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ይናገራሉ።

የአየር ንብረት ለውጥ እንዲከሰት ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል የተፈጥሮ መዛባት እና የሕዝብ ቁጥር መጨመር ተጠቃሽ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ ይህም የእርሻ መሬት ለመፈለግ ሲባል የደን መጨፍጨፍ የአየር ንብረት እንዲዛባ እንደሚያደርግ ይገልፃሉ።

በመሆኑም የተሻለ ግንዛቤ እንዲፈጠር እና የአየር ንብረት ተፅዕኖ ለመቀነስ ግብርናው ላይ በተለይ ለምግብነት የሚውሉ ማንኛውም ዓይነት ምርቶች ሲመረቱ አካባቢን በማይጎዳ መልኩ መሆን እንዳለበት ያመለክታሉ። በተጨማሪም ከተማ ለማስፋፋት ቤቶች ሲገነቡ የአካባቢ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከተፈጥሮ ጋር በማጣጣም መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።

አካባቢን መጉዳት ምን ያህል ችግር እንደሚያስከትል ለማኅበረሰቡ በማስተማር ግንዛቤ እንዲያገኙ መሠራት እንዳለበት ጠቁመው፤ በተጨማሪም የተፈጥሮ ማዳበሪያ በሰፊው አርሶ አደሩ እንዲጠቀም የሚያስችል አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን ያብራራሉ። የተፈጥሮ ሥርዓት እንዳይጎዳ ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶች መሬት ላይ ወርደው ተግባራዊ እንዲሆኑ ተቋማዊ አሠራር ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚስፈልግ ያሳስባሉ።

# ከ801 ሺህ በላይ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አዲስ አበባ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራምን ለሁሉም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ማቅረቧን የገለጹት ምክትል ከንቲባው፤ በዚህም ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ ምግብ በትምህርት ቤቶች በማግኘት ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉና ጤናቸው እንዲጠበቅ መደረጉን ገልጸዋል።

እያንዳንዱ ልጅ ለማደግና ለመማር የሚያስፈልገውን የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ የትምህርት ቤት ምግብ ፕሮግራሞች አስፈላጊ መሆናቸውንም አመላክተዋል።

ምክትል ከንቲባው፤ የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብሩ በመላ ሀገሪቱ ከሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ሕጻናትን ተጠቃሚ ያደረገ መሆኑንም ገልፀዋል። ይህ ጅምር ከፌዴራል መንግሥት በተለይም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጠንካራ ድጋፍ ማግኘቱን ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ ፈር ቀዳጅ ከተማ በመሆኗ የዚህ ፕሮግራም ስኬት በሀገር ውስጥ በማሳየቷ ለሌሎች የአፍሪካ ከተሞች አርዓያ ሆናለችም ነው ያሉት።

በማኅበረሰብ ምገባ ፕሮግራም ደግሞ ከ36 ሺህ በላይ አረጋውያን እንዲሁም ነዋሪዎች በምገባ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ ብለዋል። እነዚህ መርሐ ግብሮች የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ላይ ብቻ ሳይሆን ጤናማ እና ዘላቂ የአመጋገብ ልማዶችን በማስተዋወቅ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውንም ጠቅሰዋል።

በኢትዮጵያ የጣሊያን አምባሳደር አጎስቲኖ ፓሌሴ፣ የአዲስ አበባ ከተማ የሚላን የከተማ ምግብ ፖሊሲ ስምምነትን እ.ኤ.አ በ2021 አባል በመሆን መቀላቀሏን ጠቅሰው፤ በምገባ ፕሮግራሙ ያላትን ጠንካራ አቋም አድንቀዋል።

የአዲስ አበባ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ለከተማዋ ኩራት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ከተሞችም አርዓያ መሆኑን ተናግረዋል።

ፎረሙም የተሳካ የትምህርት ቤት ምገባ ሥራዎችን ለማሳየት፣ እንዲሁም ሁሉም ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ከተሞች ያላቸውን ሚና የሚያጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

በመድረኩ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ ከ40 በላይ የሚሆኑ የከተማ ተወካዮች፤ እንዲሁም ከጣሊያኗ ሚላን ከተማ ፖሊሲውን የሚመሩ አካላት ተገኝተዋል።

እ.ኤ.አ በ2015 የተቋቋመውና 233 ከተሞችን በአባልነት ያቀፈው የሚላን የከተማ ምግብ ፖሊሲ ስምምነት በከተሞች ውስጥ ዘላቂ የምግብ ሥርዓት አተገባበርን ለማስተዋወቅ አልሞ እየተሠራ ያለ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## እውቅናው ግብር ከፋዮች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ መነቃቃት የሚፈጥር ነው!

ከአንድ ማኅበረሰብ ተጠቃሽ ከሆኑ እሴቶች ውስጥ ጥሩ የሠራን ማበረታታት፣ መሸለም፤ ችግር ያለባቸውን መገሰጽ እና ለተግባሩ ተጠያቂ ማድረግ የተለመደ ነው። በዚህ እና ተመሳሳይነት ባላቸው የሞራል እሴቶች ትውልዶችን ኮትኩቶ ማሳደግ የአንድ ማኅበረሰብ ትልቁ ኃላፊነት ነው። ማኅበረሰባዊ መረጋጋት ከመፍጠር ባለፈ፤ የትኛውም ትውልድ በኃላፊነት መንፈስ ለራሱም ሆነ ለመጪዎች ትውልድ የተሻለ ሥራ ሠርቶ እንዲያልፉ መነቃቃትን የሚፈጥር ነው።

እንደዚህ አይነት የሞራል እሴቶች በተለይም ሃይማኖታዊ ማንነት ባለበት ማኅበረሰብ ውስጥ ከፍ ያለ ትኩረት ያላቸው፤ በማኅበረሰቡ ቀጣይ ሕልውና/ዕጣ ፈንታ ላይ ከሚኖራቸው አዎንታዊ አስተዋፅዖ አኳያም በማኅበረሰቡ ውስጥ ባሉ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊ እና መንፈሳዊ አስተምህሮዎች ውስጥ ሰፊ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው።

እነዚህ ማኅበራዊ እሴቶች ከማኅበረሰቡ አልፈው እንደሀገር ማንነት ባለው ማኅበረሰብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ የኃላፊነት መንፈስ እንዲሰርጽ በማድረግ፣ ስለ ራሱ፣ ቤተሰቡ፣ ማኅበረሰቡ እና ሀገር ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ በመፍጠር ሂደት ውስጥ የሚኖረው አስተዋፅዖ መተኪያ የሌለው ነው ።

ቀጣይነት ያለው በሥነ ምግባር የተገራ ትውልድ በመፍጠር፤ በሁለንተናዊ መልኩ የተረጋጋ ሀገር መገንባት፤ በዚህም የዜጎችን ማኅበራዊ ደኅንነት አስተማማኝ ማድረግ የሚያስችል ነው። ለሕግ እና ለሥርዓት ተገዢ የሆነ ትውልድ በማፍራትም ሠላም እና ልማት የሰፈነበት ሀገር በመፍጠር የሚኖረው አስተዋፅዖ የፍጻሜው መጀመሪያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ዓለም አሁን ላይ የደረሰችበት ሥልጣኔም ሆነ ሥልጣኔው የተገዛበት አስተሳሰብ፤ ከነዚሁ የትናንት የሞራል እሴቶች የተቀዳ፤ ዘመኑን በሚሸከም የተሐድሶ እሳቤ የተቃኘ ነው። ከሁሉም በላይ ለሕግ እና ለሥርዓት የተገዛ ትውልድን በመፍጠር ላይ ያተኮረ፤ ለራሱ፣ ለሚኖርበት ማኅበረሰብ እና ለሀገሩ በኃላፊነት መንፈስ የሚንቀሳቀስ፤ በዚህም የመንፈስ እርካታ የሚሰማው ትውልድ መፍጠር ነው ።

ከመሠልጠን ባለፈ የሠለጠነ ሀገር በመፍጠር የተሳካላቸው ሀገራት፤ የሥልጣኔያቸው ትልቁ ምስጢር ቀጣይነት ባለው መንገድ ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ መፍጠራቸው፤ ይህንን የሚያስቀጥል ጠንካራ ተቋማዊ አቅም መገንባታቸው ነው። ትውልዶች በዕለት ተዕለት የሕይወት መስተጋብራቸው ውስጥ ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ የሚያስችል ማኅበረሰባዊ ስብዕና መፍጠራቸው ነው።

ሀገራችን አብዝቶ እንደሚነገረው እና እንደሚሰማው የሃይማኖት/የሃይማኖተኞች ሀገር ከመሆኗ አኳያ፤ አብዛኞቹ መንፈሳዊ እና ከዚሁ የሚቀዱት ማኅበራዊ እና ባሕላዊ እሴቶቻችን፣ በማኅበረሰብ ውስጥ የሞራል እሳቤዎች ገዝፈው እንዲወጡ የሚያስችሉ፤ ከራሱ አልፎ ስለሌላው ወንድሙ ሆኖ ስለ ሀገር በኃላፊነት መንፈስ የሚንቀሳቀስ ትውልድ የማፍራት አቅም እንዳላቸው ይታመናል ።

ይህም ሆኖ ግን በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው እውነታ ከዚህ በብዙ መልኩ በተቃርኖ የሚታይ ነው። በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየሆነ ያለው፤ በትውልዶች መካከል በነበረው የሞራል እሴት ቅብብሎሽ ትልቅ ክፍተት መፈጠሩን በተጨባጭ የሚያመላክት ነው። ግለኝነት እና ራስ ወዳድነት፤ ሕገወጥነት እና አናርኪነት በስፋት የሚስተዋልበት ነው።

የሀገርን ብሔራዊ ጥቅሞች የሚጎዱ፤ የሕዝባችንን የእለት ተእለት ሕይወት የሚፈታተኑ ሕገወጥ ተግባሮች የሕጋዊነት ያህል በአደባባይ አቅም አግኝተው፤ ሀገር ለከፋ አደጋ፤ ሕዝብም ውስብስብ ለሆኑ ችግሮች ዳርገዋል። ከዚህ ችግር ለመውጣት የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው ቢቀጥሉም፤ ከችግሮቹ ጥልቀት እና ስፋት አኳያ ዛሬም ፈተና እንደሆኑ ነው ።

ከነዚህ ችግሮች ውስጥ በዋንኛነት የሚጠቀሰው በነጋዴው ማኅበረሰብ በስፋት የሚታየው ግብር በአግባቡ አለመክፈል ነው ። ችግሩ በዋንኛነት ለሕግ እና ለሕጋዊ ሥርዓት ካለመገዛት፣ ከተበላሸ የሞራል ስብዕና የሚመነጭ፤ ከዛም ባለፈ እንደ ሀገር ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ማበጀት ካለመቻላችን የሚነሳ ነው።

በርግጥ ካለን የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ግንባታ እና በብዙ የሞራል አስተምህሮዎች ውስጥ እንደማለፋችን ግብርን በኃላፊነት የመክፈል ጉዳይ ብዙ የሚያነጋግረን አዲስ ሀገራዊ አጀንዳ አይደለም። አብሮን ዘመናት ያስቆጠረ፣ ለሀገረ መንግሥቱ እስከ ዛሬ መቆየት እና መጽናት አቅም የሆነ ጉዳይ ነውና። ዛሬ ላይ ቆመን ለምናልማት የነገይቱ የበለጸገች ኢትዮጵያም መሠረት የሚሆን ነው።

የበለጸገች ሀገር የመፍጠሩ እውነታ ከምንም በላይ ኃላፊነት የሚሰማው እና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት መነቃቃት ያለው ትውልድ መፍጠር ስንችል እንደሆነ ይታመናል። አሁን ካለንበት ተጨባጭ እውነታ አኳያ ችግሩን ለመሻገር የወላጆችን፣ የማኅበረሰቡን እና የመንግሥትን የተቀናጀ ሥራ ይፈልጋል፤ ጊዜ ልፋት እና ድካምንም ይጠይቃል።

ይህም ሆኖ ግን ያለውን ሀገራዊ እውነታ ግምት ውስጥ በማስገባት በግብር አሰባሰብ ሂደት ኃላፊነታቸው ለመወጣት ጥረት ለሚያደርጉ ዜጎች እና ተቋማት በአደባባይ እውቅና መስጠት ከተበላሸ አሠራር ለመውጣት እንደ አንድ ስትራቴጂክ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ፤ ግብር ከፋይ ዜጎች የሚጠበቅባቸውን በተሻለ የኃላፊነት መንፈስ እንዲወጡ መነቃቃት የሚፈጥር ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከክፉ ሥራ ተቆጥበን በመልካምነት ዘመኑን እንዋጅ!

**ሶሎሞን በየነ**

አሮጌው ዘመን አብቅቶ የኢትዮጵያ አዲሱ ዓመት በተበሰረበት ወርሐ መስከረም ላይ እንገኛለን። እንዲህ አሮጌው በአዲሱ እየተተካ እልፍ ዘመንና ትውልድ አልፎ፤ እዚህ ዘመን ላይ እኛ የዛሬው ትውልድ ደርሰናል። ስንቶች ይህንን ዘመን ወይም አዲስ ዓመት ሳያዩ አልፈዋል። እኛ ግን እንደሥራችን ወይም እንደበደላችን ሳይሆን እንደ አምላክ ቸርነት ዛሬን ለማየት ታድለናል። ከዘመን ወደ ዘመን ለመሸጋገር በቅተናል። አዲስ ሕይወት ተሰጥቶናል።

የተሰጠንን አዲስ ዘመን ደግሞ የደስታ፣ የፍቅር፣ የሠላም፣ የእድገት፣ የአንድነት ... የምናደርገው እኛው ነን። በአንጻሩ ደግሞ የጦርነት፣ የመገዳደል፣ የጥላቻ፣ የመለያየት፣ የዘረኝነት ... ዘመን የምናደርገው እኛው ነን። ምክንያቱም ዘመን ማለት እኛ ነን። ስንከፋ የሚከፋ ደግ ስንሆን ደግ የሚሆን የእኛው ነጸብራቅ ነው። ለዚህ ነው አበው በአነጋጋሪ ፈላስፋ "ዘመን ማለት አንተ ነህ" ያሉት። አንተ ሠላማዊ ስትሆን ሠላማዊ ትሆናለች፡፡ አንተ ጠንክረህ ታጥቀህ ስትሠራ በዘመንህ ጎተራው ሙሉ፤ ገበያው ጥጋብ ይሆናል።

በተቃራኒው ደግሞ አንተ የከፋህ እንደሆነ ትከፋለች፡፡ በተሰጠህ ዘመን አንተ ትብስ አንቺ ትብስ ተባብሎ ተከባብሮ መኖር ካቃተህ፤ ምድር ሠላም ርቋት የጦርነት አውድማ፤ የደም ዥረት የሚወርድባት መሆና አይቀሬ ነው። በዘመንህ ሠላምህን አጥብቀህ ካልጠበቅሃት፣ ለሠላም የሚከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ ካልከፈልህ ሠላምህ ይርቅሀል። እንዲሁም በዘመንህ መግፋት መገፋትን፣ መናቅ መናናቅን፣ ማዋረድ ውርደትን፣ መጥላት መጠላትን፣ ... ያመጣል።

ከዚህ የምንረዳው ጊዜው የሚመስለው እኛን ነው። እኛ ነን ዘመኑን ደግ ወይም ክፉ የምናስብለው። "ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም" እንዲሉ አሮጌው ዘመን አልፎ የዘመን ቅብብሎሽ አዲሱ ዓመት ላይ አድርሶናል። አዲሱን ዓመት የደስታ፣ የመፈቃቀር፣ የመተሳሰብ፣ የተድላ፣ የሠላም... የምናደርገው እኛው ነን። በተገላቢጦሽ ደግሞ የኀዘን፣ የጦርነት፣ የኹከት፣ የብጥብጥ፣ ... እንዲሁ የምናደርገው እኛው ነን።

እናም ዘመን እኛ፤ እኛም ዘመን ነን። ነገር ግን ሰዎች ብዙ ጊዜ ዘመኑ ተቀይሯል፣ ዘመኑ ተበላሽቷል፣ ዘመኑ ከፍቷል፣ ... ሲሉ ይደመጣሉ። እውን ዘመኑ ተለውጧል፣ ከፍቷል፣ ተበላሽቷል፣ ተቀይሯል ....? እስኪ በሞቴ ንገሩኝ ትናንትም ሆነ ዛሬ አንድ ዓመት ከ365 ቀን ወይም ከአሥራ ሁለት ወራት ጳጉሜን ጨምሮ ተጓሎ ያውቃል? ወሩስ ከ30 ቀን ይጎላል? ሳምንቱስ ከሰባት ቀን ተቀንሶ ያውቃል? አንድ ቀን ከ24 ሰዓት ጎሎ ያውቃል? ጎሎ ከሆነ አዎ! ዘመኑ ተለውጧል፣ ተቀይሯል፣ ተበላሽቷል።

እውነታው ግን ዛሬም ሆነ ትናንት ዓመቱ ካለው ወራትና ቀናት አልተቀነሰበትም። ወሩም፣ ሳምንቱም እንዲሁም ቀኑም እንደዚያው ነው። ዛሬም ፀሐይ በምሥራቅ ወጥታ፣ በምዕራብ ትጠልቃለች፤ ጨረቃ ብርሃኗን ያለስስት ለዓለም ትለግሳለች፣ ቀንና ሌሊቱ እንዲሁ በየተራቸው ይፈራረቃሉ። ስለዚህ ብዙዎቻችን እንደምንለው ዘመኑ ተቀይሮ ወይም ከፍቶ አይደለም። እውነታው እኛ ሰዎች ከሰውነት ተራ ስንወርድ ዘመኑ ይቀየራል፣ ይቆሸሻል፣ ይበላሻል፣ ይከፋል ... እንጂ።

ትናንት አባቶቻችን ከሰውነት ውሃ ልክ ዝንፍ ሳይሉ በአንድነት፣ በፍቅር አንተ ትብስ አንቺ ተባብለው ተፈቃቅረው በይቅር ባይነት፣ በመተሳሰብ፣ በመተጋገዝ፣ ሀገርን በጋራ በመጠበቅ፣ ከልዩነቶች ይልቅ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት ቅድሚያ በመስጠት፣ በታማኝነት፣ በአርቆ አሳቢነትና አስተዋይነት፣... ወዘተ ልክ እንደ አንበሳ ተከባብረው በመኖራቸው ዘመናቸው ያማረ፣ የሰመረ ነበር። ዛሬም ያ ደጉ፣ የሠላሙ፣ የተድላው፣ የአንድነቱ፣ የተባረከው ... ዘመን እየተባለ ይታወሳል፤ ይናፈቃል፣ ይወደሳል። አባቶቻችን ሀገራችን ኢትዮጵያንም ከዜጎቿ አልፏ የጥቁር ሕዝቦች መመኪያ እንድትሆን አድርገው አልፈዋል።

"እሳት አመድ ይወልዳል" እንዲሉ የነዛ የጀግኖች፣ የታማኞች፣ የሃይማኖተኞች፣ የደጎች ልጆች ዛሬ ላይ ከሰውነት ተራ ወርደን በዘር፣ በቋንቋ ተከፋፍለን በርስ በርስ ጦርነት ምድሪቱን አኬልዳማ አደረግናት። ሕዝቡ ሠላም ወጥቶ ሠላም መግባት ልክ እንደ እንጀራ ራበው፣ እንደውሃ ጠማው። "በዓለም አደባባይ እንግዳ ተቀባይ" በመባል የሚታወቀው ሕዝብ ዛሬ ላይ ተወልዶ በአደገበት፣ ወልዶ ከብዶ ኩሎ በዳረበት ከቀዬው ባይተዋር ሆኖ ተሰደደ። በቀዬው ደመከልብ ሆኖ ቀረ። እልፍ ዜጎች በስደት የባሕር አሣ ነባሪ ሲሳይ፤ የበረሃ አውሬ እራት ሆነው ቀሩ። ኩሩው ሕዝብ በስደት ተዋረደ።

ከገዛ አብራኩ የወጡ ልጆቹ መንገድ እየዘጉ ቋንጃ ይቆርጣሉ፣ ይዘርፋሉ፣ ይገድላሉ፣ ያፈናቅላሉ። አግተው በሚሊዮን ገንዘብ ይቀበላሉ። እስኪ ንገሩኝ ዕጣ ፈንታው ደርሶ የታገተ መቼም አንዴ ታግቷል እንበል። ነገር ግን የታገተ ዘመዱን ለማስለቀቅ ገንዘብ ከጁ ቢያጣ በእድር፣ በሃይማኖት ሥፍራ፣ በጎዳና ነጠላ አንጥፎ የሰው ፊት እንደ እሳት እየገረፈው ለምኖ የተጠየቀውን ገንዘብ አሟልቶ ይዞ የሄደ ጭምር የሚታገተው ጊዜው በመከፋቱ ወይስ በመቀየሩ ነው? ይልቁንም እኛ ሰዎች ሳጥናኤል እራሱ የሚቀናብን ከፋተኞች፣ ግብዞች፣ ነፍሰ በላዎች በመሆናችን ነው። ይህንን መራራ ሐቅ እየመረረንም ቢሆን መቀበል አለብን።

እስኪ ንገሩኝ በዓይን እንኳን ሞልቶ ለማየት የምታሳሳ የሰባት ዓመት እምቦቃቅላ ሕፃን ልጅን፤ አፍና አፍንጫዋን አሽዋ ጠቅጥቆ አይሆኑ አድርጎ ደፍሮ ለመግደል ያስቻለው እውን ጊዜው ወይም ዘመኑ በመቀየሩ ነው? አይደለም ወዳጄ አትሸወድ። እውነታው እኛ ሰዎች ከሰውነት ውሃ ልክ በመውረዳችን ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ በየዘመናቱ የተነሱባት ጠላቶቿ ቅጥሯን ጥሰው፣ ድንበሯን አልፈው ካደረሱባት/ብን ሁለንተናዊ ኪሳራ በላይ በርስ በርስ ጦርነት ያወደምነው ንብረት፤ ያጣነው የእልፍ የዜጎች ሕይወት ይበልጣል። ለዚህ ደግሞ እርቀን ሳንሄድ ከሁለት ዓመት በፊት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በተካሄደው የርስ በርስ ጦርነት የወደመው ንብረት፣ የጠፋው የሰው ልጅ ሕይወት ሕያው ምስክር ነው።

ስለዚህ ሰው በዚህ ልክ ከሰውነት ተራ ወርዶ ወንድም ወንድሙን እየገደለ፣ እያፈናቀለ፣ እያሰደደ፣ አግቶ ገንዘብ እየተቀበለ፣ ሕፃናትን በጭካኔ ደፍሮ እየገደለ፣ እህት ወንድሙን በቁም ለመቅበር ሴራ እየጎነጎነ ... ቀኑ ተቀይሯል፣ ጊዜው ከፍቷል፣ ዘመኑ ተለውጧል ሊባል አይገባም። ይልቁንም ዘመኑን ዘመነ ፍዳ፣ የደም ዘመን፣ የደም ምድር፣ የግፍ መሬት ... ያደረግነው እኛው እራሳችን ነን። ምክንያቱም ዘመኑ የሚመስለው እኛን ነው።

ዘመኑ ሳይሆን እኛ እንደተቀየርን፣ ከሰውነት ተራ እንደወረድን አውቀን እራሳችን ልንፈትሽ ይገባል። የራቀን ሠላም እንዲመለስ፣ የከበበን ችግር ሁሉ ከላያችን እንደጉም ተኖ እንዲጠፋ፣ ሠላም በሀገራችን እንዲፀና፣ እድገት ልማት እንዲመጣ፣ እንደጥንት አባቶቻችን ፍቅርና አንድነት በመሐላችን እንዲጎለብት ሁሉም ጣቱን ወደሌላው ከመቀሰር ይልቅ እራሱን ሊያይ ይገባል። ሁሉም ከእኩይ ምግባሩ መታረም አለበት።

"ቀናት እየሮጡ ነው፣ ዓመታቱም እየነጐዱ ነው። ከዚህ ምድር የማልፍበት ቀን እየቀረበ ነው" ብለን እስኪ ሁላችንም እናስብና በአቅማችን የሠላም፣ የተድላ፣ የፍቅር፣ ... ዘመን በሀገራችን እንዲመጣና የተሻለች ሀገር ለተተኪው ትውልድ ለማውረስ "እንደ አቅሜ ምን እያደረግሁ ነው?" ብለን እራሳችንን ቆም ብለን መጠየቅ አለብን። ዘመናችንን እንደ ቀድሞው ደጉ ጊዜ እናድስ። ከክፉ ሥራ ተቆጥቦ ደግ ደጉን በመሥራት ዘመኑን እንዋጀው!

# ነፃ ሃሳብ

# ውስጣዊ አንድነትና ስልታዊ ምላሽ የሚሻው ትንኮሳ

ታሪኩ ዘለቀ

በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር እያስተዋልን ነው። እነዚህ ምልክቶች ከፍተኛ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትርጉም ባለው በዚህ ቀጣና የአገሪቱን ጥቅሞች ሊጎዱ የሚችሉ በከፍተኛ ጥንቃቄ (በአይነ ቁራኛ) መከታተል እንደሚያስፈልግ የሚጠቁሙ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ በቀይ ባሕርና በኤደን ባሕረ ሰላጤ የሚታየው ዓለም አቀፍ ውጥረት፣ በሱዳን ያለው የእርስ በእርስ ጦርነት፣ በአካባቢው ግብፅ እጇቿን ለማስረዘም የምታደርገው ጥረት፣ ሱማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ወዳጅነት ለማበላሸት እየሄደች ያለችበት እርቀት ተጠቃሽ ናቸው።

ከዚህ መነሻ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና የተጋረጠውን ስጋት መለየት፤ እንዲሁም ከጎረቤት አገራት ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አሁናዊ ሁኔታ መገምገምና በማያወላዳ መልኩ የማሻሻያና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። እዚህ ጋር አገራችን ከጎረቤት አገራትና በቀጣናው ልዩ ፍላጎት ካላቸው መንግስታት ጋር ከብሔራዊ ጥቅም አኳያ ያላትን ልዩነትና አንድነት በተገቢው መልኩ መለየትም ያስፈልጋል።

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ እንደሚያምነው አገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ‹‹ልማትና እድገቴን ያረጋግጡልኛል›› ባለቻቸው ሶስት ብሔራዊ አጀንዳዎች ላይ ልዩ ትኩረት አድርጋለች። የመጀመሪያው አጀንዳ ከ14 ዓመት በፊት ተጀምሮ መጠናቀቁ ሊበሰር ጫፍ ላይ የደረሰው የአባይ ግድብ የኃይል ማመንጫ ሙሉ ለሙሉ በማስጀመር ለዜጎቿ ከዚያም አልፎ ለምስራቅ አፍሪካ የኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረብ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቷን የምታሳካበት የባሕር በር ይገባኛል ጥያቄዋን በአጭር ግዜ ውስጥ ማሳካት ነው። ሌላኛውና ሶስተኛው ጉዳይ ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ቀጣና ሰላምና ፀጥታ በማረጋገጥ ለእድገቷ መሰረት የሆነ አዎንታዊ ከባቢ መፍጠር ነው።

ከእነዚህ ሶስት የአገራችን ቁልፍ ፍላጎቶች አንፃር አሁን በቀጣናው ያለው እንቅስቃሴ ስንገመግም ከፍላጎታችን በተፃራሪ የቆሙ ኃይሎችን እናገኛለን። ከዚህ ውስጥ ቀዳሚዎቹ ግብፅ፣ ሱማሌያ፣ የሱዳን የእርስ በርስ ግጭት እና የተጋጋለው የቀይ ባሕር አለመረጋጋት ላይ እሳት የሚያነዱ ቡድኖች ቀዳሚዎቹ ናቸው።

ቀደም ካሉት ዘመናት አንስቶ ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት የመሪነት ሚናዋን ስትወጣ እንደቆየች ይታወቃል። ይህንን ሚናዋን ደካማ የመንግስት መዋቅር ባለባቸው እንደ ሱማሌያ ባሉ አገራት፣ የእርስ በእርስ ግጭት በነገሰባቸው ሀገራት ጭምር (ሱዳን አብዬ ግዛት) ሰላም አስከባሪ ወታደር በመላክ ተወጥታለች እየተወጣችም ነው። ይህንን ድርሻ እየወሰደች የምትገኘው ከምንም በላይ በአካባቢው መረጋጋት ተፈጥሮ ሁሉም አገራት ወደ ልማትና እድገት እንዲገቡና ከኋላ ቀርነት መላቀቅ እንዲችሉ ነው።

የኢትዮጵያ የባሕር በር ፍላጎት ዋንኛ ምንጭም ልማት እና ሰላም ለመሆኑም ይህ ያልተቆጠበ በቀጣናው የምታበረክተው አስተዋፆ በግልፅ ያሳያል። ይሁን እንጂ አጀንዳው ሱማሊያን፣ ጅቡቲን ጨምሮ ከርቀት እጇቿን ለማስረዘም በምትጣጣረው ግብፅ አይን የተወደደ አይደለም።

በዚህ ምክንያት የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ለግጭት፣ ለድርቅ፤ ለረሀብ ለጦርነት የተፈጠረ አካባቢ እንዲሆን ተደጋጋሚ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። የግብፅ እጆች በጎረቤት አገራት በውስጥ ፖለቲካ ጭምር እየገባ ይገኛል። የኢትዮጵያን ታላላቅ የልማት አጀንዳዎች በማሰናከል ላይ የተመሰረተው ይህ እንቅስቃሴም ረዘም ላሉ ዘመናት በወዳጅነት ላይ የተመሰረተውን የጎረቤት አገራትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማበላሸት ዳር ዳር እያለ ነው። ሱማሊያ ለዚህ ጥረት በጎ ምላሽ እየሰጠች ይመስላል።

> የኢትዮጵያ መንግስት ቀጣናው ከልማትና ከሰላም ውጪ የጠብ አጫሪዎች አጀንዳ ማስፈፀሚያ እንዳይሆን ከሚያደርገው ሁለንተናዊ ዝግጅት ውስጥ ቅድሚያ ሊይዝ የሚገባው ዲፕሎማሲያዊ አማራጮችን እስከመጨረሻው አሟጦ መጠቀም ነው

ያልተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት የነገሰባት ሶማሊያ በመጠቀም ግብፅ እያደረገች ያለችው እንቅስቃሴ በበርካቶች ዘንድ ትችት እንዲሰነዘርባት አድርጓል። ግብፅ ሶማሊያን ተጠቅማ የውክልና ጦርነት ለማድረግ ግልፅ ትንኮሳዎችን እያደረገች ለመሆኑ ምልክቶች አይተናል። ለዚህ ማሳያው መርህ አልባው የሁለቱ አገራት ግንኙነት ነው። የኢትዮጵያን የልማት አጀንዳዎች ቀልብሶ ቀጣናው በተለመደው አለመረጋጋት እና ኋላቀርነት እንዲቀጥል ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ተቀጥያም ነው።

ኢትዮጵያ ለዚህ ጠብ አጫሪ ድርጊት ብስለት የተሞላበት ምላሽ እያቀረበች ቢሆንም ከድርጊቱ ላይ አይን ሳይነቀል መከታተል ያስፈልጋል። ለእያንዳንዱ የአገራቱ ትንኮሳዎች የሚመጥን ምላሽ ማዘጋጀትም ይገባል። ከሁሉ በላይ ከኢትዮጵያ አልፈው ለቀጣናው ልማትና ሰላም መረጋገጥ የሚበጁ የልማት ስራዎች (እንደ አባይ ግድብና የባሕር በር ፍላጎትን የመሰሉ) ተፈጥሯዊና ሕጋዊ መብቶች በትንኮሳ የማይቀለበሱ መሆናቸውን ማሳየት ይገባል።

የኢትዮጵያ መንግስት ቀጣናው ከልማትና ከሰላም ውጪ የጠብ አጫሪዎች አጀንዳ ማስፈፀሚያ እንዳይሆን ከሚያደርገው ሁለንተናዊ ዝግጅት ውስጥ ቅድሚያ ሊይዝ የሚገባው ዲፕሎማሲያዊ አማራጮችን እስከመጨረሻው አሟጦ መጠቀም ነው። ለዚህም የኢጋድና የአፍሪካ ሀገራት ሁኔታውን በልኩ እንዲያጤኑትና ከኢትዮጵያ ጎን እንዲቆሙ ማድረግ ነው። በተለይ ግብፅ ወደዚህ ቀጠና የምትመጣበትን ምክንያት የአካባቢው ሀገራት በአግባቡ ተረድተውት የኢትዮጵያን እውነታ እንዲቀበሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ከላይ በዝርዝር ያስቀመጣቸውን ስልታዊ አካሄዶች የኢትዮጵያ መንግስት ተግባራዊ እንዲያደርግ የውስጥ አንድነትን ማጠናከር አንደሚያስፈልግ ያምናል።

የባሕር በር ጥያቄም ይሁን ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ብሔራዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ ዲፕሎማሲ ቁልፍ ጉዳይ ቢሆንም ቀዳሚው ግን ውስጣዊ አንድነትን ማጠናከርና ሉአላዊ ጉዳዮች ላይ ዘብ ለመቆም መዘጋጀት ነው። በሕዳሴው ግድብ ላይ የታየው ፅናትም ለዚህ በቂ ማሳያ መሆን ይችላል። ቁርጠኛ የሆነ የምሁራንና የፖለቲከኞ የፀና አቋም ግድቡ በድል ለመጠናቀቁ መሰረት ነበር። ይህንን ውስጣዊ አንድነትና የጋራ መግባባት በሌሎች ብሔራዊ አጀንዳዎቻችን ላይ መድገም ይገባናል። የውስጥ ሰላም ማስፈን ተቀዳሚ ተግባር ሆኖ በተጓዳኝ ደግሞ ለቀጠናው ሰላም መሆን ኢትዮጵያ ያላትን ሚና ማሳየት ይጠበቅባታል። የኢትዮጵያ መንግስትም ለዚህ ስልት ስኬታማነት ውጤታማ የሆኑ የውጪ ግንኙነት ማእቀፎች ላይ አበክሮ መስራት አለበት።

ኢትዮጵያ የባሕር በር ይገባኛል ፍላጎቷን ለማሳካት የምታደርገው ሕጋዊና ስልታዊ አካሄድ ያልተዋጠላቸው፤ የአባይ ግድብ አይናቸው እየተመለከተ መጠናቀቁና የእድገት ምንጭ መሆኑ እንደ ውስጥ እግር እሳት የሆነባቸው፤ በቀጣናው ግዙፍ ኃይል ለመሆን እየተንደረደረች መሆኑ የሚያንገበግባቸው ግብፅን የመሰሉ አገራት ምስራቅ አፍሪካ እንዳይረጋጋ ቀን ከሌት እየሰሩ ነው። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን እጆቻችንን ለልማት ስናነሳ፣ ይህንን መሰል እክል አንደሚገጥም ጠፍቶን አለመሆኑን መሰናክሉን አልፈን በምናስመዘግበው ስኬት ማሳየት ይገባናል።

ከሁሉም በላይ በአፍሪካ ቀንድ የኢትዮጵያን የማይናዋጥ አቋም የማስገንዘብ ስራ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ መቀጠል አለበት። በተለይ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያላት ቁርኝትም አሁን ካለው ከፍ ማድረግ የሚያስችል የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማከናወን ተገቢ ነው። የዲፕሎማሲ ስራው ከንግግርና ከወረቀት የተሻገረ በድል የሚገለፅ ሊሆን ይገባል።

ኢትዮጵያውያን የአባይ ግድብ ግንባታን በፍፁም ፍላጎትና አንድነት ስንጀምር እጃችንን የሚጎትቱ ትርክቶችን በማንሳት የስልጣኔ ጭራ ሊያደርጉን ተረባርበዋል። የመጀመሪያ ያረጀውና ያፈጀውን ‹‹ነባሩን የግብፅ የብቸኛ ተጠቃሚነት ትርክት ‹ሁሉንም ጠቅልሎ የመውሰድ እሳቤ› መጣስ አትችሉም›› የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ‹‹በራሳችሁ አቅም የግድቡን ግንባታ እውን አታደርጉትም›› የሚል ነበር። ሁለቱም ትርክቶች መሰረታቸው ውሸት ቢሆንም ለዘመናት በመደጋገማቸው እንደ እውነት ተቆጥረው ነበር።

ይሁን እንጂ በአባይ ግድብ ዙሪያ እጃችንን አሳስረው ለማስቀመጥ ያደረጉት ተደጋጋሚ ሙከራ ሊሳካ አልቻለም። ኢትዮጵያውያን አይቻልምን በማፍረስ እውን አድርገው ለዓለም አሳይተዋል። ይህ ተግባር ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ከማስደንበሩም በላይ አሁን በቀጣናው ለመቅበዝበዛቸው ምክንያት ሆኗል። በየትኛውም ስሌት ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ታላቅ ኃይል ሆና እንዳትወጣ፤ በቀይ ባሕር ላይ ተፅዕኖዋ ጎልቶ እንዳትታይ የሚፈልጉት እነዚህ አካላት የተለያዩ ስልቶችን እየተከተሉ ይገኛሉ። ከዚህ ውስጥ በሱማሊያ በኩል የጀመሩት ረብ የለሽ ሙከራ ተጠቃሽ ነው።

ይህንን ሕልማቸውን በአባይ ገድብ ግንባታ ላይ እንዳደረግነው ሁሉ ዳግም ልናከሽፈው ይገባል። ፈተናዎችን ተቋቁመን ከእቅዳችን ዳር የደረስነው በሕብረታችንና በአንድነታችን መሆኑን መገንዘብ አለብን። በአባይ ግድብ ዙሪያ የማይበጠስ ጠንካራ አንድነት አሳይተን ‹‹ግድቡ የኔም ነው›› ብለን ባንነሳ ለዛሬ ድል ባልበቃን ነበር። ለዚህ ነው ዛሬም በምስራቅ አፍሪካ ሊኖረን ለምንሻው ጠንካራ ክንድ ዳግም ሕብረት የሚያስፈልገን። የጠላቶቻችንን የሴራ ጉንጉን ለመሻገር ቀጣናውን የተረጋጋና ለሁለንተናዊ እድገት ምቹ እንዲሆን ውስጣዊ አንድነታችንን ማጠንከር ይገባናል።

ዛሬም ሌላ የሕዳሴ ፕሮጀክት አለን፤ ይህ አጀንዳ የባሕር በር ባለቤት መሆን ነው። በቀደመው የኢትዮጵያ ታሪክ የባሕር በር የነበርንና በሴራ የተነጠቅን ሕዝቦች መሆናችን ፀሀይ የሞቀው ሀቅ ነው። አሁን ህጋዊ፣ ተፈጥሯዊ መብታችንን ተገን አድርገን እውን ልናደርገው ይገባል። ይሁን እንጂ ቀላል ፈተና እየገጠመን አይደለም፤ በቀጣናው ልዩ ፍላጎት ባላቸው አካላት ጉሸሚያ እየደረሰብን ነው። ለዚህ ነው ሕብረታችን የሚያስፈልገው።

የአባይ ግድብ ሲጀመር የነበረ ውክቢያና ማስፈራሪያ ዛሬም በተመሳሳይ ቀጥሏል። ለዚህ ውክቢያ እና ማስፈራሪያ ጆሮ ሰጥተን ቢሆን ግድቡን ከዳር ባላደረስነው ነበር። በተመሳሳይ እየተደረገ ላለው ትንኮሳና ዛቻ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ አይሆንም። ትኩረት አለመስጠት ግን በንቃትና በጥንቃቄ በቀጣናው የሚታየውን ትንኮሳ አለመከታተል እንዳልሆነ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት።

ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናት። የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ምሳሌ እና ተፅእኖ ፈጣሪ ሀገር። በአፍሪካና በምትገኝበት የምስራቅ አፍሪካ ቀጣናው ያላት ተፅእኖ ፈጣሪነት ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ደግሞ የባሕር በር ጥያቄዋ ምላሽ ሊያገኝ ይገባል። ለስኬቱም ‹‹የባሕር በር ባለቤትነት ጥያቄ ለድርድር የማይቀርብ ብሔራዊ ጥቅማችን›› መሆኑን ግልፅ በማድረግ በጋራ ልንቆም ይገባል። ሕብረታችን ሲፀና፣ አንድነታችን ሲጎለብት ደግሞ ማንኛውም ብሔራዊ ጥቅማችንን መሰረት ያደረገ ጥያቄ ሁሉ መልስ ያገኛል!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ማኅበራዊ ሚዲያና የአዕምሮ ጤና

ክብረአብ በላቸው

የአዕምሮ ጤና ሰዎች ስለሚያስቡት፣ ስለሚሰማቸው እና በዚህም ስለሚያሳዩት ባህሪ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የአእምሮ ጤና ሰዎች የሕይወት ውጣውረድን ተቋቁመው እንዲኖሩ፣ ችሎታቸውን እንዲገነዘቡ፣ እንዲማሩና እንዲሰሩ እንዲሁም ለማህበረሰባቸው አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ የሚያስችል የአእምሮ ደህንነት ነው።

ይህ የአዕምሮ ጤና ሲቃወስ ደግሞ የግለሰቡን የየዕለት ተግባር፣ ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እና የሰውነት ሁኔታ ላይም ተጽዕኖ እንዳለው ይገለጻል፡፡ ማህበራዊና የገቢ ሁኔታ፣ ጥሩ ያልሆኑ የልጅነት ልምዶች፣ አፈጣጠርና መሰረታዊ የጤና ሁኔታዎች የአንድን ሰው የአእምሮ ጤንነት ሊወስኑ እንደሚችሉም ነው የሚነገረው። የአእምሮ ሕመም ዓይነቶች ጭንቀት፣ የስሜት መለዋወጥ (መቃወስ) እና ስኪዞፍሬኒያ (ከእውነታው ዓለም መዛባት) ናቸው፡፡ ጭንቀት የተለመደ የአእምሮ ሕመም ነው ይባላል፡፡ ይህ የአዕምሮ ጭንቀት ያጋጠማቸው ሰዎች ከአንዳንድ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ከፍተኛ ፍርሃት አለባቸው።

የጭንቀት ምልክቶች ከሚባሉት ውስጥ እረፍት ማጣት፣ ድካም፣ ትኩረት አለማድረግ፣ የጡንቻ ሕመምና የተቆራረጠ እንቅልፍ ይጠቀሳሉ፡፡ የስሜት መለዋወጥ (መቃወስ)፤ ከፍተኛ ደስታና ከፍተኛ ጭንቀት ሲፈራረቅ የሚስተዋል የአዕምሮ ሕመም ዓይነት ነው፡፡

በአዕምሮ ሕመም ተፅዕኖ በኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት በአፍላ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሰሩ ጥናቶች ያሳያሉ። ከዓለም የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ተያይዞ ዲጂታል ሚዲያው በአዕምሮ ጤና ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ብዙዎች ያነሳሉ።

ዲጂታል ሚዲያው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ በፍጥነት ያደገ፣ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ በቢሊዮን በሚቆጠሩ የዓለማችን ሰዎች ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ይህ ማለት ደግሞ እራሱን የቻለ ማህበራዊ፣ ሥነ ልቦናዊና አዕምሮአዊ ከፍተኛ ጉዳት ይዞ የሚመጣ ነው።

አሁን አሁን የማህበራዊ ሚዲያ ሰፊ ቁጥር ላላቸው ታዳጊዎች የእለት ተእለት ሕይወታቸው አካል እየሆነ መጥቷል፡፡ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያላቸው ግንዛቤ እና ጥገኝነት ከብዙ ጎልማሶች እጅግ የላቀ ከመሆኑ ባሻገር፣ ማህበራዊ ሚዲያዎችንም በከፍተኛ ፍጥነት እየተጠቀሙ ነው። ዓለም እጅግ ውስብስብና ዲጂታል እየሆነች በምትሄድበት እያንዳንዷ ቅጽበት የታዳጊዎችም ሕይወት እንደዚያ እየሆነ መሄዱ የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዘግይቶም ቢሆን የአእምሮ ጤና መታወክ ያስከትላል፡፡

እንደ ተመራማሪዎች ጥናት ከሆነ ማህበራዊ ሚዲያ በታዳጊዎች ዘንድ እንደሱስ የመሆን እድሉ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ተመራማሪዎች በጥናታችን መሰረት አንዳንድ የአእምሮ ክፍሎች ታዳጊዎች ማህበራዊ ሚዲያ ላይ በሚያገኟቸው "likes" ንቁ እንደሚሆኑና ይህ ደግሞ በመልሱ የማህበራዊ ሚዲያ ፍላጎታቸው እንዲጨምር እንደሚያደርጋቸው ደርሰንበታል ይላሉ፡፡

ታዳጊዎች በተለይም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በሚለጥፏቸው የራሳቸው ፎቶዎች ላይ ብዙ (ላይኮችን) በሚመለከቱበት ጊዜ ከበርካታ የአእምሮ ክልሎቻቸው በተጨማሪ አበረታች የአንጎል አካል የሆነው ኒውክሊየስ አከመንስ ንቁ ይሆናል፡፡ ይህ የአንጎል አካባቢ የምንወዳቸውን ሰዎች ፎቶ ስናይ ወይም ገንዘብ ስናሸንፍ ምላሽ የሚሰጠው ተመሳሳይ ክልል ነው፡፡

በነገራችን ላይ ይህ የአእምሮ ክፍል በታዳጊነት ወቅት ይበልጥ ስሜታዊ መሆኑ ስለምን ታዳጊዎች በማህበራዊ ሚዲያ ሱስ እንደሚጠለፉ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ታዳጊዎች ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማስፋት እና ጠቃሚ የቴክኒክ ክህሎቶችን እንዲማሩ ለመርዳት ማህበራዊ ሚዲያዎች ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ ጥርጥር የለውም፡፡ ጥያቄው ግን እነዚህ ማህበራዊ ሚዲያዎች በታዳጊዎች ጭንቅላት ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ያሳድራሉ? የሚለው ነው፡፡

ታዳጊዎች ለአእምሮ መጋለጥ የሚዳረጉት ብዙ ጊዜአቸውን ኦንላይን ስለሚያሳልፉ ብቻ አይደለም፡ ፡ ይልቁንስ ኦንላይን የሚሆኑበትን ጊዜ መቆጣጠር ስለማይችሉ በዛ ያለ ጊዜ ኦንላይን ሆነው ባሳለፉ ጊዜ በዚህ በአእምሮ ጭንቀት የመጠቃት እድላቸው ሰፋ ይላል፡ ፡ ብዙ ጊዜን ኦንላይን ማሳለፍ ደግሞ ዞሮ ዞሮ ለበርካታ የጤና እክሎች መዳረጉ አይቀሬ ነው፡፡



ጥናቶችን መሰረት በማድረግ ስንመለከት በዓለም አቀፍ ደረጃ አምስት ቢሊዮን የሚሆን ሕዝብ የዲጂታል ሚዲያ ተጠቃሚ ነው፡፡ በኢትዮጵያም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዜጋ የዲጂታል ሚዲያ ተጠቃሚ ነው። ከሀገሪቱ የሕዝብ ቁጥር አብዛኛውን ድርሻ የሚይዘው ደግሞ በዚህ የሚዲያ ተፅዕኖ ውስጥ ያለ ወጣት በመሆኑ እንደ ሀገር ጉዳቱ ቀላል እንዳልሆነ እሙን ነው።

ከጤና አንፃር ከ10 እስከ 19 ዓመት ያሉት ታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶችን ስንመለከት ይህ የዕድሜ ክልል የአዕምሮ ዕድገታቸው የሚያድግበት ግዜ ነው፤ ወቅቱ ታዳጊዎች ነገሮችን የሚያዩበት የአዕምሮ ክፍላቸው የሚያድግበት ሰዓት ነው። ለአብነት ተለዋዋጭ ስሜቶች፣ ከሰው ጋር ያለ መግባባት፣ እያንዳንዱ ባህርያቸው የሚቀያየርበት ወቅት በመሆኑ ትልቅ ጥንቃቄ የሚያስፈልግበት የዕድገት ደረጃ እንደሆነ ይታመናል።

``የወጣትነት ዕድሜ በውስጣችን ያለውን የሚሰማንን ነገር ሁለት ጊዜ ሳናስብ የምናወጣበት ወቅት ነው'' የሚሉ የሥነ ልቦና ባለሙያዎች፤ በባህርይ የእኛነት ስሜት የሚሰማበት፣ ትንሽ ነገር ቶሎ የሚያበረታታበትና በዛው ልክ ጥቂት ነገር ቶሎ የሚያስከፋበት አደገኛ ዕድሜ በመሆኑ ይህንን ተረድቶ ማለፍ የሚያስፈልግ እንደሆነ ያነሳሉ።

የማህበራዊ ሚዲያ ከመጀመሪያው ሲመጣ የንግድ ሀሳብ ይዞ፣ ብዙ ሰዎች ይሳተፉበታል የሚለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመጣ ነው። ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር በእጅ ስልካቸው እያቀረበ ገንዘብ ማግኘት ነው ዋና ዓላማው፡፡ ከዚህ አንፃር የሚዲያ አማራጩ ወጣቶችንና ሕፃናትን ዓላማ አድርጎ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ በአጠቃላይ የሚሰጠው ጥቅም እንዳለ ሆኖ የሚያመጣው ችግርም ከፍተኛ ነው።

አንድ ወጣት በማህበራዊ ሚዲያ ቀርቦ እያወራ ወይም ፎቶውን እያጋራ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ደግሞ ያለ ገደብ ማንኛውም ሰው ሊያየው የሚችለው በመሆኑ ተመልካቹ ያንን ሰው ሊያበረታታውም ወይም ሊጎዳው ይችላል፡፡ ሴት ከሆነች ሰውነትሽ አያምርም፣ መልክሽ ቀፋፊ ነው እያለ በቀላሉ ማንኛውም ሰው የከፋት አስተያየት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ከፍተኛ መጨናነቅ፣ ድብርት፣ አለፍ ሲልም እራስን እስከማጥፋት የሚችል የሥነ አዕምሮ ምስቅልቅል ውስጥ የሚከት በመሆኑ ሁሌም ቆንጆ ሆኖ ለመታየት ከአቅም በላይ በሆኑ ነገሮች ላይ ግዜ ማጥፋት ይመጣል ይህም ሌላ የሥነልቦና ጉዳት ይዞ የሚመጣ ይሆናል።

የእኔን ልጥፍ (ፖስት) ብዙ ሰው አየልኝ ወይም ወደደው፣ ወይም ብዙ ሰው አልተመለከተውም የሚለው ነገር ወጣቶቹን በጣም የሚያስጨንቃቸውና ውድድር ውስጥ የሚከታቸው በመሆኑ የራሳቸው

**ዓለም እጅግ ውስብስብና ዲጂታል እየሆነች በምትሄድበት እያንዳንዷ ቅጽበት የታዳጊዎችም ሕይወት እንደዚያ እየሆነ መሄዱ የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዘግይቶም ቢሆን የአእምሮ ጤና መታወክ ያስከትላል**

ማንነት ያልሆነውን ግን ሰዎች ሊወዱት ይችላሉ ብለው የሚያስቡትን ነገር ማሳየት ይጀምራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ድባቴ ውስጥ በመክተት እራሳቸውን እንዲጎዱ ሊያደርግ የሚችል የአዕምሮ ጤና ችግር ውስጥ የሚያስገባቸው ነው።

እንደ ዘርፉ ባለሙያዎች ገለፃ፤ ወጣቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከኮምፒውተር እና ስልካቸው ጋር በመሆኑ ምግባቸውን እንኳ ለመብላት የሚሆን ሰዓት ስለሌላቸው የአመጋገብ ስርዓት መዛባት ይከተላል። ይህንን ተከትሎ ለሚመጡ የአዕምሮ ጤና ችግሮች ተጋላጭ ይሆናሉ።

ለረዥም ሰዓት እንቅልፍ ሳያገኙ የሚቆዩ ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ ነው፤ አዕምሯችን በተፈጥሮ እንቅልፍ የሚተኛበት ሰዓት ጨለማ የሚሆንበት ወይም ብዙ ብርሃን በማይኖርበት ሰዓት እንደመሆኑ፤ ማህበራዊ ሚዲያው ደግሞ አዕምሯችን መተኛት ባለበት ሰዓት ላይ ጠብቀን እንዳንተኛ ስለሚያደርገን ሕይወታችን እንቅልፍ ማጣትን ተከትሎ ለሚመጡ የጭንቀት፣ የስሜት መራበሽ፣ የሀዘን ስሜቶች ወይም ሕመሞች ተጋላጭ ያደርገናል።

በተጨማሪም ወጣቶች ለብዙ ሰዓት በአንድ ቦታ ተቀምጠው ስለሚውሉ አለመንቀሳቀሳቸው በራሱ እርሱን ተከትለው ለሚመጡ እንደ የልብ ሕመም ላሉ በሽታዎች ተጋላጭ ይሆናሉ። አዕምሮአችን እንቅስቃሴ ባላደርግን ቁጥር የደም ዝውውሮችን የአዕምሮ ንቃታችንን ሊያመጣ ስለማይችል ጫናዎች ተደራራቢ በሆኑ ቁጥር እስከ አዕምሮ ደም መፍሰስ ሊያደርስ የሚችል ሕመም ሊከሰትብን ይችላል።

በሌላ በኩል ወጣቶችና ሕፃናት አብዛኛውን ሰዓት ትምህርታቸውን ከማንበብ ይልቅ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ስለሆነ የዕውቀት አድማሳቸው የጠበበ ይሆናል፡፡ ከዛ ባለፈ ትምህርት ቤት ሄደውም በማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ስር ሆነው አካዳሚያዊ ከሆነው ነገር ይልቅ በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎች ስላዩት ወይም ስላጋጠማቸው ነገር በማውራት ነው የሚያሳልፉት፡፡ ይህ እጅግ አደገኛ በመሆኑ የሚያስከትለው ጉዳት እንደ ሀገር በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

የዲጂታል ሚዲያው መቆጣጠር የምንችለው አይደለም የሚሉት ባለሙያዎች፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ሀገራት የሚቸገሩበት ጉዳይ ነው። ታዳጊ ሀገር ላይ ሲሆን ደግሞ ተፅዕኖው ከፍተኛ ይሆናል፤ ወላጆች ስለዲጂታል ሚዲያው የሚኖራቸው ግንዛቤ አነስተኛ ስለሆነና ጉዳትና ጥቅሙን በትክክል የመገንዘብ እጥረት ስላለ ችግሩ የሰፋ ይሆናል ይላሉ።

ይህንን ችግር ለመቀነስ እንደ ሀገር ፖሊሲዎች ሊኖሩን ይገባል የሚሉት የዘርፉ ባለሙያዎች፤ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ፖሊሲ ኖሮ በተለይ ሕፃናት በቀላሉ እንዳይጠቀሙ ወይም ዕድሜያቸውን ባገናዘበ መልኩ መጠቀም እንዲችሉ እንደ ሀገር መመሪያዎች ያስፈልጉናል። ከሌሎች ሀገራት ልምድ በመውሰድ ተደራሽ መሆን የሌለባቸው የዲጂታል ሚዲያ አማራጮች እንዲገደቡ መንግሥት ሀገር ተረካቢ ትውልድ እንዳይጠፋ መስራት እንዳለበት ይናገራሉ።

ዲጂታል ሚዲያው ሰዎች በማንነታቸው፣ በቆዳ ቀለማቸው፣ በአፈጣጠራቸውና ባላቸው ተፈጥሮ የሚሰደቡበትና የሚንቋሸሹበት መድረክ በመሆኑ፤ ይህ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና ተፅዕኖ የሚያሳድር ነው፡፡ ይህንን ለመከላከል እንዲያስችል ሁለት ወገኖች ማለትም ወላጅ እና ልጅ በስምምነት ስለ ጉዳትና ጥቅሙ የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር መጠቀም ያለባቸውንና የሌለባቸውን የሚዲያ አይነቶች ላይ ገደብ መጣል የሚቻል በመሆኑ በዚህ መንገድ ቴክኖሎጂው የሚያደርሰውን ከፍተኛ የሆነ ዘርፈ ብዙ ጉዳት መቀነስ ይቻላል።

በስም ከሚታወቁ የማህበራዊ ሚዲያዎች አማራጮች በተጨማሪ በይፋ የማይታወቁ ነገር ግን ኢትዮጵያን ጨምሮ በመላው ዓለም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተከታይ ያላቸው የበይነመረብ ሚዲያዎች እንዳሉ ይታወቃል፤ እነዚህ ሚዲያዎች የተቃኙት ሕፃናትና ወጣቶችን መሠረት በማድረግ ስለሆነ የሚለቋቸው የምስል፣ የድምፅና የቪዲዮ መረጃዎች በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚፈልጉት ግን የማያስፈልጋቸው በመሆኑ፤ በዚህ ከቁጥጥር ውጭ በወጣ የሚዲያ አጠቃቀም ብዙዎች ለስነአዓምሮ ሕመም ተጋላጭ እንደሚሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ።

በጣም በቤት ውስጥ በማህበራዊ ሚዲያ ተገድቦ የሚኖር ልጅ ምን እየሰራ እንደሆነ ወላጆች አብረው ሆነው በየቀኑ በግልፅነት የሚያወሩበት ጊዜ እንደሚያስፈልግ የሚናገሩት ባለሙያዎች፤ ከዚህ ውጭ ወላጆች ልጆቻቸው በአካል ሄደው ከሰዎች ጋር ማውራት፣ መጫወት እንዲችሉ መንገድ መፍጠር እንዳለባቸው ይመክራሉ።

በተጨማሪም ወላጆች ወጣት ልጆቻቸው በማህበራዊ ሚዲያ ስለሚያገጥሟቸው ነገሮች በግልፅ ከቤተሰብ ጋር እንዲያወሩ ማድረግ አለባቸው፤ ይህ በማህበራዊ ሚዲያ ታዳጊ ወጣቶች የእርቃን ፎቶግራፎቻቸውን እንዲልኩ የሚጠየቁበት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ይህንን ተከትሎ ከሚመጣ ፈተና ለማምለጥ እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል ይላሉ።

አሁን በኢትዮጵያ ዲጂታል ሚዲያን ተጠቅሞ የሚፈፀም ጥቃት እያደገ የሚሄድ እንጂ የሚቀንስ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ መንግሥት የተለያዩ የሕግና የፖሊሲ መመሪያዎችን በማውጣት ያሉትን ደግሞ በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓት እንዲኖር መስራት ይጠበቅበታል።

**• ይህንን ጽሁፍ ስናጠናቅር ከጽሁፍ መረጃዎች ባሻገር የተለያዩ ድረገጾችን እና የማህበራዊ ሚዲያ አውታሮችን በምንጭነት ተጠቅመናል**

# የምድር በረከት

# ዩኒቨርሲቲው ያመላከታቸው የኦፓል ማእድን ማልማት ሂደት ተግዳሮቶችና መፍትሄዎች

ፍሬሕይወት አወቀ



በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ማዕድናትን የመለየትና አልምቶ ለመጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎች በሰፊው እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አኳያ በማእድን ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማቱ እየከተናወነ ካለው ተግባር በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲዎች እና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚከናወኑ ተግባሮችም ይጠቀሳሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች በማእድን ዘርፉ ጥናትና ምርምር በማድረግ የዘርፉን እምቅ ሀብት አልምቶ ለመጠቀም አስቻይ ሁኔታዎችን በማመላከት ላይ ይገኛሉ፡፡ በማዕድን ዘርፍ ጥናትና ምርምር በማድረግ የድርሻቸውን እየተወጡ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የወሎ ዩኒቨርሲቲ አንዱ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በደቡብ ወሎ ደላንታ አካባቢ በስፋት በሚገኘው የኦፓል ማዕድን ላይ ጥናት በማድረግ የምርምር ሥራ ሰርቷል፡፡ በተለይም በደላንታ አካባቢ ባደረገው ጥናት የዘርፉን እምቅ ሀብቶች ጠቁሟል፤ ማእድኑን በማልማት ሂደት እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በመለየትም መፍትሄዎችንም ማመላከት ችሏል፡፡

በወሎ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ዶክተር ሲሳይ አወቀ እንዳሉት፤ በዩኒቨርሲቲው አስተባባሪነት በደቡብ ወሎ አካባቢ የሚገኙ የማዕድን አይነቶች ልየታ የሚል ቡድን ተዋቅሮ የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ጥናቱ ትኩረት ካደረገባቸው መካከል በደቡብ ወሎ ደላንታ ወረዳ በስፋት የሚገኘው የኦፓል ማዕድን አንዱ ነው፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ጥናቱ በማዕድን ዘርፉ በተለይም በኦፓል ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን መለየትና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ አሰራሮችን እንዴት መፍጠር ይቻላል የሚሉና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

በመጀመሪያ በአካባቢው ያለውን የኦፓል ማዕድን ማህበረሰቡ አልምቶ ለመጠቀም ያጋጠሙት ችግሮች ምንድናቸው የሚሉትን መለየት ተችሏል፡፡ በዚህም ማዕድኑን ለማውጣት ቁፋሮ የሚደረግበት መንገድ አንዱና ዋነኛው ችግር እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ ቁፋሮው የሚከናወነው ባህላዊ በሆነ መንገድ፣ በተጣበበና ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታም ከስድስት መቶ እስከ ሰባት መቶ ሜትር ወደ ውስጥ ይቆፈራል፡፡ ይህም ሕይወት ማጣትን ጨምሮ ለጤና መታወክና ለሌሎች አደጋዎች ተጋላጭ እንደሚያደርግ ጥናቱም አመላክቷል፤ ማዕድኑን ለይቶ ካለማወቅ የተነሳም ለብክነት ሊጋለጥ የሚችልበትን ሁኔታም ጠቁሟል፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብ ማዕድኑን አልምቶ ለመጠቀም አስፈላጊና ወሳኝ የሆኑ ዘመናዊ መሣሪያዎች ማለትም መቆፈሪያ፣ መነጽር፣ ጓንት፣ የአፍ መሸፈኛና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች እንደሌለው ጠቅሰው፣ ይህ በመሆኑም ማዕድኑን አልምቶ መጠቀም እንዳልቻለ ዶክተር ሲሳይ አስረድተዋል፡፡

ማህበረሰቡ የተለያዩ ችግሮችን ተቋቁሞ የሚያገኘውን ማዕድን ወደ ገበያ ይዞ ሲወጣ የሕገወጦች ሲሳይ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰው፣ ይህም ሌላው የዘርፉ ችግር መሆኑን ጥናቱ ማመላከቱን ጠቁመዋል። ዶክተር ሲሳይ እንዳሉት፤ አልሚዎቹ በብዙ ድካም ያገኙትን ማዕድን ገበያ ይዘው ሲወጡ ከተማ ሳይደርሱ መንግሥት የማያውቃቸው ሕገወጥ ነጋዴዎች ርካሽ በሆነ ዋጋ ይቀበሏቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ኦፓሉን ለማውጣት የሚጠቀሙባቸው መቆፈሪያዎች ባህላዊ በመሆናቸው ሊሰባበሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡ አልሚዎቹ የኦፓል ማዕድኑን የሚይዙበት መንገድም ሌላው ችግር ነው፡፡ ኦፓል ከወጣ በኋላ የሚቀመጥበት መንገድ ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባል፡፡ ማህበረሰቡ ግን ይህን ሲያደርግ አይስተዋልም። በዚህ የተነሳም ማዕድኑ ለጉዳት እየተጋለጠ ይገኛል፡፡ ኦፓል በተፈጥሮው ብርሃን የሚፈልግ ባለመሆኑ ለጸሐይ ብርሃን ሲጋለጥ ሊሰባበር የሚችልበት ሁኔታ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ወደ ገበያ ይዘው የሚወጡት ኦፓል የተበላሸና ለከፍተኛ ብክነት የተጋለጠ ይሆናል፡፡

በደቡብ ወሎ ደላንታ አካባቢ ብቻ ከ30 በላይ የኦፓል ማዕድን የሚያወጡ ማህበራት እንዳሉ የጠቀሱት ዶክተር ሲሳይ፤ በእያንዳንዱ ማህበር ውስጥም ከ12 እስከ 20 የሚደርሱ ወጣቶች ተደራጅተው ኦፓሉን እንደሚያወጡ ተናግረዋል፡፡ ማህበራቱ ኦፓሉን ለማውጣት ወደ ጉድጓድ ውስጥ የሚገቡት በተራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከአንደኛው ማህበር አምስትና ስድስት ሆነው ገብተው ማዕድን ሲያገኙ ሌሎቹ ደግሞ በተራቸው ገብተው ሲቆፍሩ ውለው ማእድኑን ሳያገኙ የሚወጡበት ሁኔታ እንዳለ፣ በአንጻሩ ደግሞ በቀጣዩ ቀን ደግሞ ሌሎች ቆፍረው ሊያገኙና ሸጠውም ሊጠቀሙ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ ተናግረዋል፡፡ ይህ አሰራር ሁሉንም የማህበሩን አባላት ተጠቃሚ ማድረግ ያላስቻለ ስለመሆኑ በጥናቱ ማረጋገጥ መቻሉን አስታውቀዋል፡፡

ማዕድን ለማውጣት ከፍተኛ የሆነ ቁፋሮ የሚካሄድ በመሆኑ የመሬት መንሸራተት ሊያጋጥም የሚችል ስለመሆኑም በጥናቱ ተረጋግጧል ያሉት ዶክተር ሲሳይ፣ በመሬት መንሸራተቱ ምክንያት በሰውና በእንስሳት ላይ አደጋ እንደሚያጋጥም ተናግረዋል፡፡ የመንገድ መዘጋትና ሌሎች ችግሮችንም በአካባቢው ላይ ሊያስከትል እንደሚችል ጠቅሰው፣ በቁፋሮ የሚወጣው አፈር ሊኖረው በሚችለው አሲዳማነት ሳቢያም የአካባቢው መሬት ምርታማነት እየቀነሰ ይገኛል ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ለልማቱ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ባህላዊ መሆናቸው ምርታማነቱ እንዲቀንስ እያደረገ መሆኑንም ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል ጉድጓዱ እየራቀ ሲሄድ አፈር ወደ ውጭ ለማውጣት ብዙ ጊዜና ጉልበት የሚወስድ በመሆኑ ወጣቶቹን ተጠቃሚ አያደርግም፡፡ እነዚህንና መሰል ችግሮችን በጥናቱ መለየት ተችሏል፡፡ ችግሮቹን ከመለየት ባሻገርም የመፍትሔ አቅጣጫ መመላከቱንም ዶክተር ሲሳይ ተናግረዋል፡፡

ማዕድኑን አውጥቶ ለመጠቀም በርካታ ችግሮች መኖራቸውን ጠቅሰው፣ ችግሮቹን ለመፍታት በዋናነት ቴክኖሎጂን መጠቀም የግድ ነው ብለዋል፡፡ ማዕድኑ በማይባክንበት መንገድ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማዕድኑን ማውጣት አስፈላጊና አማራጭ የሌለው መፍትሔ እንደሆነ ለሚመለከተው አካል መቅረቡንም አስታውቀዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በክልሉ፣ በዩኒቨርሲቲ፣ በወረዳና በዞን ደረጃ እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉ ተግባራትን በመለየት በአካባቢው የተደረገው የመጀመሪያው ዙር የኦፓል ማዕድን ጥናት መጠናቀቁን አመልክተዋል፡፡

በሁለተኛው ዙር የተደረገው ጥናትም እንዲሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኦፓል ከሌሎች አገራት ጋር ሲነጻጸር ምን ደረጃ ላይ ነው በሚል ደረጃ መስጠት የሚያስችል ጥናት ተካሂዷል ያሉት ዶክተር ሲሳይ፤ በወሎ ደላንታ ውስጥ ከሚገኙ ስምንት ቦታዎች መካከል ሁለት ቦታዎች ለናሙና ተወስደው ጥናት እንደተደረገባቸው አስታውቀዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ቦታዎችም ሁሉንም አይነት ኦፓሎች ሊወክሉ የሚችሉ በመሆናቸው ዘመናዊ

**ማዕድኑን ለማውጣት አስፈሳጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በማዕድን ዘርፍ እየተስተዋለ ያለው ብክነት ቴክኖሎጂን ካለመጠቀም የመጣ ስለመሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል**

መሳሪያዎችን በመጠቀም የኦፓሉን ባህሪያት መለየት ተችሏል ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ኦፓል በሁለት አይነት መንገድ ይለያል፡፡ አንደኛው መንገድ መልኩን በማየት ነው፡፡ በዚህም ከጸሐይ ብርሃን ጋር በሚኖረው መስተጋብር የሚፈጠረውን ማንጸባረቅ በማየት ይለያል። ኦፓል የጌጣጌጥ ወይም የውበት ቁስ ስለሆነ ውበት ይሰጣል ወይስ አይሰጥም የሚለውን በአይን በማየት መለየት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ መለየት ነው፡፡ ለዚህም አውስትራሊያ ተጠቃሽ ስትሆን፤ ሀገሪቱ ዘመናዊ መሳሪያ በመጠቀም ለኦፓሎቹ ደረጃ አውጥታለች፡፡ ስለዚህ እነሱ የተጠቀሟቸውን መሳሪያዎች በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ኦፓሎች አውስትራሊያ ካለው ኦፓል ጋር ሲነጻጸሩ የትኛውን ደረጃ ሊይዙ ይችላሉ የሚል ጥናት ተደርጎ አበረታች ውጤት ተገኝቷል ሲሉ ዶክተር ሲሳይ አስታውቀዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ በወሎ ደላንታ አካባቢ የሚገኘው ኦፓል አውስትራሊኖች ከፍተኛ ደረጃ ብለው ካስቀመጡት የኦፓል አይነት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል ብለዋል፡፡

ጥናቱ በክልሉ የሚገኘውንና ከፍተኛ ደረጃ ያለውን የኦፓል ማዕድን የአካባቢው ማህበረሰብ አልምቶ መጠቀም የሚችልበትን መንገድም አመላክቷል፡፡ ለአብነትም ኦፓልን የሚያወጡ ሰዎች ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግና ኦፓሉን በአካባቢው አሰውቦና አስጊጦ ለገበያ ማቅረብ የሚያስችል ማዕከል ማቋቋም የሚለው አንድ መፍትሄ ነው፡፡ በዚህ በኩል ቴክኒክና ሙያ ላይ የተጀማመሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል ቢችሉ ዘርፉን አልምቶ የመጠቀም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይቻላል የሚሉ ምክረ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

እነዚህን አጠናክሮ ለማስቀጠልና በአካባቢው ተጨማሪ ሥራዎችን መስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም ሲሉ ዶክተር ሲሳይ አስገንዝበዋል፡፡ በጥናቱ የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት ብሎም የማዕድን ዘርፉ በተለይም የወሎ ደላንታ ኦፓልን አልምቶ መጠቀም እንዲቻል የተሰሩ ሥራዎች ቢኖሩም መሬት የወረደ ሥራ እየታየ አይደለ ብለዋል፡፡

ለዚህም በአንድ ወቅት ተከስቶ የነበው የኮቪድ ወረርሽኝ አንደኛው ምክንያት መሆኑን አመልከተው፣ በሰሜኑ ክልል የተፈጠረው ጦርነትም እንዲሁ ሌላው አካባቢው ላይ ተጨማሪ ሥራ እንዳይሰራ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡ ያም ሆኖ ክልሉ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱን አመላከተዋል፡፡

ጥናቱ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት ከተከናወኑ ተግባሮች መካከል የኦፓል የገበያ ማዕከልን ለመገንባት የተጀመረ ሥራ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር ፣ በደቡብ ወሎ ደላንታ ወገን ጤና ከተማ ላይ የኦፓል ገበያ ማዕከል የተቋቋመ ቢሆንም እስካሁን ተግባራዊ መሆን አልቻለም ብለዋል፡፡ በአካባቢው ያለው የኦፓል ማዕድን ከፍተኛ ሀብት መሆኑን ጠቅሰው፣ የማስተዋወቅ ሥራ በመሥራት የግል ባለሀብቱን በመሳብና ሀብቱን ጥቅም ላይ የማዋል ሥራ ተጠናክሮ ሊሠራበት ይገባል ብለዋል፡፡

እርግጥ ነው የማዕድን ልማት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ይጠይቃል ያሉት ዶክተር ሲሳይ፤ የተሟላ መሰረተ ልማት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል፡፡ ከዚህ ውጭ አካባቢውን ለኢንቨስትመንት ምቹ የማድረግ ሥራ በመስራት የግል ባለሃብቱን ወደ አካባቢው ማምጣትና የኦፓል ማዕድንን በስፋት አልምቶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል አስገንዝበዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ማዕድን የማይተካና አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ ከዋለ መልሶ ማግኘት የማይቻል ውድ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የተፈጥሮ ሃብቶችን ደግሞ በአግባቡ መጠቀም ይገባል፡፡ «ማዕድንን ያለአግባብ ከመጠቀም ፈጽሞ አለመጠቀም ይሻላል» ሲሉ አስገንዝበው፣ እንዲህ አይነት የተፈጥሮ ሀብቶች የዜጎች ሃብት እንደመሆናቸው በአግባቡ ተጠብቀው አቅምና እውቀት እንዲሁም ቴክኖሎጂ ሲኖር መጠቀም ይገባል ሲሉ መክረዋል፡፡ ይህ ሲሆን አገሪቱንም በተሻለ መልኩ ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል ባይ ናቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ከአቅምና ከዕውቀት እንዲሁም ከቴክኖሎጂ ውጭ መጠቀም የማዕድን ሃብቱን ለብክነትና ለብልሽት ከመዳረግ ባለፈ የሚያስገኘው ጥቅም የለም፡፡

እንደ ዶክተር ሲሳይ ማብራሪያ፤ ዘርፉ የሚሰጠውን ጥቅም መሰረት በማድረግ መጠቀም ከተፈለገም ዘርፉ የሚጠይቀውን ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጪ ማውጣት ይገባል፤ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ባለው የመንግሥት መዋቅር ማዕድንን በምን አግባብ መጠቀም እንደሚቻልና ከማዕድኑ መንግሥትና ሕዝብ የሚያገኙት ጥቅም ምን እንደሆነ በመለየት ሕጎችን አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ማዕድኑን ለማውጣት አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በማዕድን ዘርፍ እየተስተዋለ ያለው ብክነት ቴክኖሎጂን ካለመጠቀም የመጣ እንደሆነ በጥናቱ ተመላክቷል ብለዋል፡፡

የተገኘውን ማዕድንም እንዲሁ ቦታውን ሳይለቅ ባለበት ቦታ ላይ እሴት መጨመር የሚቻልበትን የስልጠና ማዕከል ማቋቋም እንደሚገባ አስገንዝበው፣ በስልጠና ማዕከላቱ ማእድን አውጪዎቹን እንዲሁም የሚያስውቡና የሚያስጌጡትን ባለሙያዎች ማሰልጠን ያስፈልጋል፡፡ ይህም በዘርፉ የሚስተዋለውን ሕገወጥ እንቅስቃሴ ለመገደብ አማራጭ መሆኑን ዶክተር ሲሳይ አመልክተው፣ እነዚህንና መሰል ጥረቶች ማድረግ ከተቻለ ማህበረሰቡ ማዕድኑን አልምቶ መጠቀምና አገርም ከዘርፉ መጠቀም እንደምትችል ተናግረዋል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የእናት እውነት

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)

ከእኔና ከእማዬ ማን እንደሚበልጥ በቅርብ ነው ያወኩት፡፡ እማዬ እናቴ እንደሆነች የገባኝ ብዙ ዘግይቼ ነው፡፡ ታላቅ እህቴ ነበር የምትመስለኝ፡፡ ጡቷን እየጠባሁ አድጌ፣ በክንዷ ታቅፌ፣ በጀርባዋ ታዝዬም እናቴ አትመስለኝም ነበር፡፡ መንገድ ላይ ከእናቴ ጋር ያየን መንገደኛ እህትማማች እንደሆንን ከማሰብ ባለፈ ምንም ነገር አስቦ አያውቅም፡፡ በቁመት እኩል ነን..ከኔ የዘለለ.. እንደ እናት ሩቅ የሆነ ሀሳብ ስታስብ አይቻት አላውቅም፡፡ ግን በኔ ውስጥ የትም ቦታ ነበረች፡፡ የትም ቦታ አገኛታለሁ፡፡ እሷ የሌለችበት ምንም ነገር አልነበረኝም፡፡ እኔም በእናቴ ሁሉም ቦታ አለሁ፡፡ በእኔ ሁሉም ቦታ ውስጥም አለች፡፡

ሩሃማ ነው ስሜ..ሩሃማ ያለችኝ እናቴ ናት፡፡ ምሕረት የሚገባት ሴት ማለት ነው፡፡ እናቴ እሷ በተራመደችበት የዘመን ሰርጥ ውስጥ እንዳልራመድ ስትል ነው ሩሃማ ያለችኝ፡፡ እሷ ያየችውን የዘመን ነውር፣ የጊዜ ኩነኔ እንዳላይ ስትል ነው ሩሃማ ያለችኝ፡፡ በእኔ ሩሃማነት ውስጥ የእሷ ያለፈ ታሪክ ሲታደስ አይቻለሁ፡፡ እኔ ፊት እናቴ ሁልጊዜም አዲስ ናት፡፡ በእኔ ኃጢያት..በእኔ መተላለፍ ልትቆሽሽ የማይገባሽ ነፍስ ነሽ ስትል ሩሃማ.. ምሕረት የሚገባሽ ሴት አለችኝ፡፡ የአባት ዕዳ ለልጅ እንደሚባለው የእናቴ የዘመን ጸጸቶች እኔ ላይ አርፈው እንዳያሰቃዩኝ ምሕረት የሚገባት ሴት አለችኝ፡፡

እናቴ ታሪኳን ስትነግረኝ ምን ያክል ስህተት ብትሠራ ነው የዚህን ያክል ትላንትን የተጸየፈችው እያልኩ አስባለሁ፡፡ አንድ ቀን አስራ ሁለተኛ ዓመቴን ባከበርኩበት ሠልስት ድንገት በተኛሁበት ልብሴ በደም ረጥቦ አየሁት.. እየጮሁኩ ወደ እናቴ ሮጥኩ፡፡ ትታደገኛለች ብዬ ሳስብ በእኔ መከራ ውስጥ እናቴ ስትስቅ አየኋት፡፡ በእናቴ አዲስ ባሕሪ ነፍሴ ተረበሸች..ሳላውቀው በእናቴ ላይ ተስፋ የቆረጥኩበት የመጀመሪያው ቀን ያን ቀን ነበር፡፡ እናቴን ሳውቃት ተስፋዬ ነበረች፡፡ ለእግሮቼ የወርቅ ምንጣፍ፣ ለክንዶቼ ጌጣም አልቦ፣ ለሴትነቴ ዘውድና ማዕረግ ስትሆን አይቻት አውቃለሁ፡፡ በደም በጨቀየሁበት ያን ቀን ግን ሳቀችብኝ፡፡ ሳቋ ብዙ አልቆየም..ፊቴ ተንበረከከችና አቀፈችኝ፡፡ ለምን እና እንዴት እንደደማሁ ሳይገባኝና ሳይገባት ‹የኔ ቆንጆ አደግሽልኝ..› ብላ ጉንጮቼን በደስታ ሳመቻቸው፡፡ ሁሉም ነገር ግራ ገብቶኝ ነበር፡፡ ልብሴ ላይ ያለው ደም በየት በኩል እንዴት ሆኖ እንደመጣ ሳላውቅ የእናቴ በደስታ መፍነክነክ ጤንነቷን እንድጠራጠር አደረገኝ፡፡

ፊቷ ላይ አለቀስኩ..እናቴን ፈራኋት፡፡ ያቀፉኝን ክንዶቿን፣ የሳመኝን ከንፈሯን ተጠራጠርኩት፡፡ ለዘላለም ሲራራልኝ የነበረውን እናትነቷን ሰጋሁት፡፡ እቅፏ ውስጥ እያለፉ ልሸሻት ስታገላት ‹የኔ ቆንጆ..ምንም አልሆንሽም እሺ..ይሄ ተፈጥሮ ላንቺና ለእኔ የሰጠችን ፀጋችን ነው› ብላ ድጋሚ ሳመችኝ፡፡

አሁንም አልገባኝም..ስለምን እንደምታወራ አልገባኝም፡፡ ራሴን ከእቅፏ ለማውጣት ተናነኳት ወደ ደረቷ ስባ ይበልጥ እያቀፈችኝ ‹እኔ እያለሁ አንቺ ምንም አትሆኚም..እኔ እያለሁ የሚጎዳሽ ክንድ የለም፡፡ ሩሃማዬ ነሽ፡፡ ነፍስሽ መጽናኛዬ ናት› አለችኝ፡፡

እናቴ እንደዛ ቀን ግራ ገብታኝ አታውቅም፡፡ ምን እንደሆንኩ ትነግረኛለች ብዬ ስጠብቅ ምንም ባልመሰለው እናትነት እቅፏ ውስጥ አስቀረችኝ፡፡ በተንበረከከችበት ወደ ላይ አንጋጣ ዓይኖቼን ፈለገቻቸው፡፡ ዓይኖቼን ስታስተውላቸው ቆይታ እንባ አቀረረች፡፡ ለቅሶዋ አስፈራኝ..ከሳቋ መልስ መነፍረቋ የሆነ ነገር እንደሆንኩ እንዳስብ አደረገኝ፡፡ ለቅሶዋ አስለቅሶኝ ጉያዋ ውስጥ ነፈረኩ፡፡

‹የኔ ቆንጆ ደስታ እኮ ነው የሚያስለቅሰኝ፡፡ ስላደግሽልኝ..ሴት ስለሆንሽልኝ ደስ ብሎኝ እኮ ነው› አለችኝ እያለቀሰ በሚፈግ ፊት፡፡ ተረጋጋሁ..ምንም እንዳልተፈጠረ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ግን ልቤ እየፈራ ነበር፡፡ ልቤ ውስጥ ያለውን አንድ መዓት ጥያቄ ተረድታ ብትመልስልኝ ስል በማሰብ ተረጋጋሁ፡፡

‹ልብስሽን የነካሽ ደም የፀጋ ደም ነው..

ከማለቷ ‹ምንም አልሆንኩም? አልታመምኩም? ስል በፈራ ስሜት ጠየኳት፡፡

‹ምንምአልሆንሽም..የማደግሽ..የመሠልጠንሽ ምልክት ነው፡፡ ሴት ልጅ እንዲህ እንዳቺ ደም ሲደማት ለኃላፊነት፣ ለእናትነት እየተዘጋጀች ነው ማለት ነው፡፡ እናም አሁን አንቺ እናት ለመሆንና ኃላፊነት ለመሸከም ተዘጋጅተሻል ማለት ነው› አለችኝ፡፡

አስራ ሁለት አመቴን ባከበርኩበት ሰልስት በተኛሁበት ያስደነገጠኝ ደም የልዕልና ምልክት እንደሆነ እናቴ ስትነግረኝ..ስለደሜ ለጓደኞቼ ለመናገር ቸኮልኩ፡፡ ከአሁን አሁን ከእናቴ እቅፍ ውስጥ ወጥቼ ወደሚያንጃብቡብኝ ወንዶች በመሄድ በመሽኮርመም ሴት እንደሆንኩና ለእናትነት እንደተዘጋጀሁ ላበስራቸው ተጣደፍኩ፡፡ እናቴ ግን እንዲህ አለችኝ ‹አሁን ተጠንቀቀሽ የምትኖሪበት እድሜ ላይ ነሽ፡፡ ይሄ ደም የክብር ደም ነው፡፡ አለችኝ በደም ወደረጠበው ቀሚሴ እየጠቆመች፡፡

ከእናቴ አፍ አዲስ ነገር ሰማሁ፡፡ እንባዋን አድርቃ ሳቋን አምቃ ለሴትነቴ እንግዳ የሆነ ነገር ትነግረኝ ጀመር፡፡ ለራሴ አዲስ ሆኜ በእናቴ ፊት ራሴን አገኘሁት፡፡

‹ይሄ ደም የሴትነትሽ ጌጥ ነው፡፡ የውበት፣ የአፍላነት አሸንክታብ፡፡ በስሌት ከኖርሽ ወደነገ ያደርስሻል በስሜት ከኖርሽ ደግሞ ነገሽን ይቀማሻል፡፡ ይሄ ደም አንቺን ጠንካራና አስተዋይ የሚያደርግሽ እንጂ የትም ለማንም ራሽን የምትገልጪበት አይደለም፡፡ ይሄ ደም ለባልሽ መልካም ሚስት፣ ለልጆችሽ ጥሩ እናት የሚያደርግሽ የተፈጥሮ ቃል ኪዳንሽ ነው፡፡ ይሄ ደም ከስሜት አርቆ በስሌት ፍኖት ላይ ወደነገሽ፣ ወደምትናፍቂው ሕልምሽ የሚያስጠጋሽ እንጂ ጠልፎ የሚጥልሽ እንዳይሆን ራሽን ጠብቂ፡፡ አለችኝ፡፡

በእናቴ ምክር ነፍሴ በልቤ ውስጥ ገለሞተች፡፡ ሰንኮፌን እየጣልኩ እንደምትለኝ አይነት ሴት እየሆንኩ ራሴን አገኘሁት፡፡ እናቴ ነግራኝ የምሸረው እውነት የለኝም፡፡ በእኔ ውስጥ አለች የለ? በእሷ ውስጥም መኖር እፈልጋለሁ..ያላባራ የእናቴ አደራ ከአሳቤ አደናቀፈኝ፡፡ ወደ ምክሯ ሸፈትኩ፡፡

‹ከዚህ ደም በኋላ አንቺን ሽተው፣ ውበትሽንና ሴትነትሽን ተመኝተው በውሸት አፍ የክብር ቀሚስሽን ለመግለብ በዙሪያሽ የሚያንጃብቡ ወንዶች ብዙ ናቸው፡፡ እኔ አንቺን በአስራ አንድ ዓመቴ የወለድኩሽ ሕይወትን የሚያስተምረኝ መምህር አጠገቤ ስለሌለ ነው፡፡ በዛ የመጀመሪያውን ደሜን ባየሁበት ልጅነቴ ውስጥ ሕይወትን የሚያስተምረኝ ሰው ቢኖር ኖሮ ከሕልሜ ርቄ በምንምነት ውስጥ አልገኝም ነበር፡፡ አሁን አንቺም የምልሽን ስሚ.. ከዚህ ደም ቀጥሎ ሌላ ሴትነት፣ ሌላ ክብር አለሽ እዛ ክብርሽ ላይ እስክትደርሺ የማንም ሳትሆኚ የራስሽና የሕልምሽ ብቻ በመሆን እንድትኖሪ አደራ እልሻለሁ፡፡ ያኔ ሩሃማዬ ትሆኛለሽ..ያኔ ያጣሁትን ክብሬን በአንቺ ውስጥ አየዋለሁ› ስትል ያልተሳመ ጉንጬን ሳመችኝ፡፡

በእናቴ መሳም ውስጥ ነፍሴ ያልተረዳቸውን አንድ መዓት ጥበብ ሸመተች፡፡ ነፍሴ የተመኘችው እውነት ይሄ ነበር፡፡ ይሄ ደም የኃላፊነት ደም እንደሆነ ገባኝ..ከዛ ደም በኋላ እናቴ እንዳለችኝ ተጠንቅቄ መርገጥና ተጠንቅቄ መኖር ጀመርኩ፡፡

ከዛ ደም በኋላ ከእናቴ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋወኩ..

# ዓለም አቀፍ

## ባይደን እና ኔታንያሁ በኢራን ላይ ስለሚፈጸመው ጥቃት መከሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እና የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ እሥራኤል በኢራን ላይ ልትወስደው ስላቀደችው የአጸፋ ጥቃት መከሩ።

ሁለቱ መሪዎች ለ30 ደቂቃ በስልክ ባደረጉት ምክክር የአጸፋ ጥቃቱ ተገቢነት ላይ መስማማታቸውን ዋይትሐውስ ገልጿል።

እሥራኤል ከባላንጣዋ ኢራን በቅርቡ ለደረሰባት የባላስቲክ ሚሳኤል ጥቃት ምን አይነት አጸፋዊ እርምጃ እንደምትወስድ አልተገለጸም።

ፕሬዚዳንት ባይደን ባለፈው ሳምንት እሥራኤል የኢራን የነዳጅ እና የኒዩክሌር ጣቢያዎች እንዳታጠቃ ጥሪ ማቅረባቸው ቢነገርም ቴል አቪቭ የቴህራንን የኒዩክሌር ጣቢያዎች ዒላማ ልታደርግ እንደምትችል ይጠበቃል።



የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኔታንያሁ እና የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባይደን

ተንታኞች እሥራኤል የኢራንን የባላስቲክ ሚሳኤል ማምረቻ ጣቢያዎች እና የአየር መቃወሚያ ሥርዓቶች ልትመታ እንደምትችል መናገራቸውን ሬውተርስ ዘግቧል።

የእሥራኤሉ መከላከያ ሚኒስትር ዮቭ ጋላንት “የእኛ (እሥራኤል) ጥቃት እልቂት የሚያስከትል፣ ዒላማውን የሚመታና ከሁሉም በላይ የማይጠበቅ ይሆናል” ማለታቸውን የእሥራኤል መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል።

ኢራን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ በኩል ከእሥራኤል የሚቃጣ የአጸፋ እርምጃ ከባድ ዋጋ ያስከፍላል ስትል መዛቷ የሚታወስ ነው።

እሥራኤል በሊባኖስ ከሄዝቦላህ ጋር የምታደርገው የምድር ውጊያ እና በቤሩትና ሌሎች ከተሞች የምትፈጽመው የአየር ጥቃትም ባይደን እና ኔታንያሁ ከመከሩባቸው ጉዳዮች መካከል ይገኙበታል።

ፕሬዚዳንት ባይደን በዚሁ ወቅት እስራኤል በሊባኖስ የሚፈጸመው የአየር ጥቃት በንጹሐን ላይ የሚያደርሰው ጉዳት እንዲቀንስ አሳስበዋል ብሏል ዋይትሐውስ ባወጣው መግለጫ።

በተያያዘ ዜና እሥራኤል በቤሩት የምትፈጸመው የአየር ጥቃትና በደቡባዊ ሊባኖስ የሚካሄደው ውጊያ ቀጥሎ ወደ ሶሪያም ተሻግሯል።

የእስራኤል የጦር ጄቶች በሶሪያ በኢራን ድጋፍ ይደረግላቸዋል በተባሉ ቡድኖች እና የሄዝቦላህ አባላት ላይ ጥቃት ማድረሳቸውን የሀገሪቱ ጦር ገልጿል።

በሶሪያ ቁኔትራ በተባለ አካባቢ በተፈጸመ ጥቃት የሄዝቦላህ ክንፍ የሆነው “ጎላን ቴረሪስት ኔትወርክ” አባል የሆነውና ለሄዝቦላህ መረጃ የሚያቀብለው አድሃም ጃሁት ተገድሏል ብሏል ጦሩ ባወጣው መግለጫ።

የሶሪያ ብሔራዊ ቴሌቪዥን በበኩሉ እሥራኤል በሆምስ እና ሃማ ከተሞች አቅራቢያ የተፈጸሙት የአየር ጥቃቶች “መጠነኛ የንብረት ውድመት” ማስከተላቸውን ዘግቧል።

እስራኤል በኢራን ይደገፋሉ የምትላቸው የፍልስጤም፣ የሊባኖስ፣ የሶሪያ፣ የየመን እና የኢራቅ ታጣቂ ኃይሎች የተቀናጀ ጦርነት ከፍተውብኛል ብላ ታምናለች። በጋዛ ከሃማስ ጋር ጦርነት ከጀመረች አንስቶም በሶሪያ እና የመን ተደጋጋሚ የአየር ጥቃቶችን ማድረሷ ይታወሳል።

## ቱርካዊው ፓይለት በረራ ላይ እያለ ሕይወቱ አለፈ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ከአሜሪካ ወደ ቱርክ ሲጓዝ የነበረ የመንገደኞችን አውሮፕላን እያበረረ የነበረ ቱርካዊ ፓይለት በበረራ ላይ ሳለ ታሞ ሕይወቱ አለፈ።

ፓይለቱ ከአሜሪካዋ ሲያትል ወደ ቱርኳ ኢስታንቡል በረራ ላይ በነበረበት ወቅት ነው አየር ላይ ሕይወቱ ያለፈው።

የ59 ዓመቱ ካፒቴን ኢልሺን ፔህሊቫን አውሮፕላኑን እያበረረ በነበረበት ወቅት ራሱን በመሳቱ ሁለተኛው ፓይለት እና ረዳት አብራሪው አውሮፕላኑን መቆጣጠራቸውን የአየር መንገዱ ቃል አቀባይ በኤክስ ገጻቸው ገልጸዋል።

“በአውሮፕላኑ ውስጥ ለፓይለቱ የመጀመሪያ እርዳታ ቢደረግለትም ሳይሳካ ቀርቷል። የአውሮፕላኑ አብራሪዎች በድንገተኛ ሁኔታ ለማረፍ ጥረት ቢያደርጉም ፓይለቱ በአየር ላይ እያለ ሕይወቱ አልፏል” ሲሉ ያህያ ኡስተን ገልጸዋል።

የቱርኩ አየር መንገድ ንብረት የሆነው ኤርባስ ኤ 350 አውሮፕላን ኒውዮርክ ላይ እንዲያርፍ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚያም መንገደኞቹን ወደ ቱርክ ለማብረር ዕቅድ ተይዞ እንደነበር ቃል አቀባዩ አክለዋል።

የበረራ ቁጥር ቲኬ 204 የሆነው አውሮፕላን ከሲያትል የተነሳው በሀገሬው ሰዓት አቆጣጠር ማክሰኞ ምሽት 1 ሰዓት አካባቢ ነበር።

አብራሪው በካናዳዋ ግዛት ኑናቩት ሕመም ማጋጠሙን ተከትሎ ባልደረቦቹ አውሮፕላኑን ተረክበው ወደ ጆን ኤፍ ኬኔዲ አየር ማረፊያ አቅንተዋል።

አውሮፕላኑ ከሲያትል ከተነሳ ከስምንት ሰዓታት በኋላ በኒውዮርክ አርፏል።

ከአውሮፓውያኑ 2007 ጀምሮ የቱርክ አየር መንገድ አብራሪ የነበረው ኢልሺን ፔህሊቫን መደበኛ የጤና ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን፣ ሥራቸውን ሊያስተጓጉል የሚችል ምንም ዓይነት የጤና እክል እንዳልነበራቸው አየር መንገዱ ገልጿል።

የቱርክ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ማኅበር፣ ታትካ ፓይለቱ ለበርካታ ዓመታት የአቪዬሽን ማኅበረሰቡን እንዳገለገለ አስታውሶ ለቤተሰቦቹ፣ ለወዳጆቹ እና ለሥራ ባልደረቦቹ መጽናናትን ተመኝቷል።

ፓይለቱ ሕይወቱ ያለፈበት ምክንያትም ሆነ ሕመም እስካሁን አልተገለጸም። አብራሪዎች በየ12 ወሩ መደበኛ የሕክምና ምርመራዎችን የሚያደርጉ ሲሆን፣ ዕድሜያቸው ከ40 በላይ የሆናቸው ፓይለቶች ደግሞ በየስድስት ወሩ የሕክምና የምስክር ወረቀታቸውን ማደስ አለባቸው።

በአውሮፓውያኑ 2015 የአሜሪካ አየር መንገድ ፓይለት ከፊኒክስ ወደ ቦስተን በሌሊት እየበረረ በነበረበት ወቅት ራሱን ስቶ በረራ ላይ ሕይወቱ አልፏል።

የ57 ዓመቱ ፓይለት ራሱን መሳቱን ተከትሎ ሌላኛው አብራሪ አውሮፕላኑን ተረክቦ በሲራኩስ ግዛት በድንገተኛ ሁኔታ አርፏል።

በአሁኑ ወቅት በመንገደኞች አውሮፕላን ሁለት አብራሪዎች በአብራሪዎች ክፍል ውስጥ መገኘት አለባቸው።

ሆኖም የአውሮፓ ኅብረት የአቪዬሽን ደኅንነት ኤጀንሲ በበረራ ወቅት አንድ ፓይለት ትልልቅ የመንገደኞች አውሮፕላኖችን በብቸኝነት ለማብረር የሚያስችል ቴክኖሎጂ እየተሠራ ነው ብሏል።

የአውሮፓ ኮክፒት ማኅበር እና ሌሎች የፓይለቶች ማኅበራት በአውሮፕላኖች ውስጥ ያሉ አብራሪዎችን ቁጥር መቀነስ ደኅንነትን አደጋ ላይ ይጥላል በማለት ጅማሮውን ተቃውመዋል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ቡሳ ጎኖፋ- የመረዳዳትና ፈጥኖ የመድረስ ባህላዊ እሴት

**ዳግም ከበደ**

በመስከረም 25 እና 26 ቀን 2017 ዓ.ም የተከበረውን የኢሬቻ ባህላዊ በዓል አስመልክቶ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን በስካይ ላይት ሆቴል የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንት ኤግዚቢሽን ለሦስት ቀናት ማካሄዱ ይታወሳል። በኤግዚቢሽኑ ላይ የክልሉ የቱሪዝም መስህቦች፣ የቱሪዝም ዘርፍን የሚያሳዩ ተግባራትና በርካታ የክልሉ ባህላዊ እሴቶች ቀርበው ተዋውቀዋል፡፡ ባንኮችና የቴክኖሎጂ ተቋማትም በኢግዚቢሽኑ ተሳትፈዋል፡፡

የገዳ ስርዓት አንዱ እሴት የሆነው የቡሳ ጎኖፋ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴትም በአውደ ርዕይው ቀርቦ ለታዳሚያኑ ቀርቦ እንዲተዋወቅ ተደርጓል። የዝግጅት ክፍላችን የዚህን አገር በቀል ባህላዊ ስርዓት ምንነት፣ ጠቀሜታና አጠቃላይ እሴቶቹን በዛሬው ›ሀገርኛ› አምድ ላይ ይዞ ቀርቧል፡፡

ወይዘሮ ኤልዳና ሱሌማን በቡሳ ጎኖፋ የኦሮሚያ የኮሙኒኬሽንና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ምክትል ኃላፊ ነች። እሷ እንደምትለው፤ ቡሳ ጎኖፋ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እንደ አንድ የአደጋ መከላከል ተቋም የሚሰራ ሲሆን፣ ከዚያም ያለፉ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ማእቀፎች በመያዝ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

ቡሳ ጎኖፋ የሚለውን ስያሜ ያገኘው ከኦሮሞ የገዳ ስርዓት ነው። በገዳ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እንዲሁም ባህላዊ ጉዳዮች የሚፈፀሙባቸው እሴቶች አሉ። ከእነዚህ ወስጥ ቡሳ ጎኖፋ የሚል ስያሜ ያለው የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሳቤም አንዱ ነው።

የኦሮሞ ብሄረሰብ የተፈጥሮ፣ የሰው ሰራሽና ሌሎችም በሕይወት ኡደት ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮች ሲያጋጥሙት አንደ ሕዝብ መልሶ እንዲያገግምና ወደ ቀድሞው (ከዚያም በተሻለ ሁኔታ) ይዞታው እንዲመለስ የሚያደርግበት ስርዓት ቡሳ ጎኖፋ ይባላል። በዚህ እሳቤ (በቡሳ ጎኖፋ ስርዓት) በማህበረሰቡ ውስጥ ጉዳት የደረሰባቸው፣ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች በድንገተኛ ድጋፍ የማገዝ፣ የጠፋው ሀብት ንብረታቸውን መልሰው እንዲያገኙ የመርዳት፣ በስነ ልቦናና በጤና ጉዳይ ከሚገጥማቸው እክል ድነው መልሰው እንዲቋቋሙ የማድረግ ተግባር ይፈፀማል።

እንደ ምክትል ኮሙኒኬሽን ኃላፊዋ ገለፃ፤ ቡሳ ጎኖፋ በገዳ ስርዓት ውስጥ ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁነቶችን በአንድ ላይ አቅፎ የያዘ ነው። ከእነዚህ ወስጥ ደግሞ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳዮችን በስፋት ይዳስሳል።

በኦሮምኛ ቋንቋ ቡሳ ማለት በፍጥነት የሚለውን የአማርኛ ፍቺ ይወክላል። ይህም ማለት በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ አንድ ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት በስርዓቱ አማካኝነት የድጋፍ ማሰባሰብ አድርጎ ምላሽ መስጠት ላይ የሚያተኩር ነው።

ጎኖፋ የሚለው የኦሮምኛ ቃል ደግሞ በድንገተኛ አደጋ ንብረቱን አሊያም ሌሎች ሀብቶቹን ያጣ ሰው በጊዜያዊነት ከተደረገለት ድጋፍ ባሻገር በቋሚነት የሚቋቋምበት መንገድን የሚወክል ነው። በጥቅሉ ቡሳ ጎኖፋ በማህበረሰቡ ውስጥ የደረሰን አደጋ በአጭር ጊዜም ሆነ በዘላቂነት በመመከት መፍትሄ መስጠት ላይ ትኩረቱን ያደርጋል።

‹‹ሰዎች ደንገተኛ አደጋ ገጥሟቸው ሀብት ንብረታቸውን ሊያጡ ይችላሉ›› የምትለው የኮሙኒኬሽን ምክትል ኃላፊዋ ወይዘሮ ኤልዳና፤ አደጋውም ከኢኮኖሚ ጫና ያለፈ የሞራል ስብራት፣ የቤተሰብ መበተን ሊያስከትል እንደሚችል ትገልፃለች። ለምሳሌ ያህል በኦሮሞ ብሄረሰብ ውስጥ አንድ መቶ ከብቶች ያሉትና ኑሮውን በጥሩ ሁኔታ ሲመራ የነበረ የአንድ አካባቢ ነዋሪ በድንገተኛ አደጋ ሁሉንም ከብቶች ቢያጣ በቡሳ ጎኖፋ የገዳ ባህላዊ ስርዓት እያንዳንዱ ጎረቤትና የመንደሩ ነዋሪዎች ካላቸው ከብቶች አንድ አንድ በማዋጣት 99 የሚሆኑትን በመተካት ተጎጂውን ወደነበረበት የኑሮ ደረጃ የመመለስ ግዴታ እንዳለባቸው ትናገራለች።

ይሁን እንጂ ይህ ስርዓት ከ100 ከብቶች ውስጥ 99 የሚሆኑትን በመተካት አንዷን ከብት በመጨመር 100 የማይደፍንበት ምክንያት ‹‹አንዷ የእግዚአብሄር ነች፤ ወይም በእግዚአብሄር የምትተካ ነች›› የሚል እሳቤ ስላለው እንደሆነም ታብራራለች። ይህን መሰል የመተጋገዝና የመተባበር እሴት በኦሮሞ ብሄረሰብ የገዳ ስርዓት ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የነበረና አሁንም ድረስ ተጠብቆ የቆየ መሆኑን ታነሳለች። በዚህ ምክንያት የተፈጥሮም ይሁን የሰው ሰራሽ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት የማህበረሰቡ አባላት ከሀብት ንብረታቸው እንዳይጎሉ፤ ስነ ልቦናቸው እንዳይጎዳና ተስፋ እንዳይቆርጡ ከለላ የሚሆን ባህላዊ እሴት መሆኑን ትገልፃለች።

በኦሮሞ ባህል ውስጥ ልመና ነውር መሆኑን የምትናገረው ምክትል ኃላፊዋ፤ አንድ ሰው ተቸግሮ ጎረቤቱ የተደላደለ ኑሮ መኖሩና ለማገዝ ፍላጎት አለማሳየቱም እንዲሁ የተወገዘና ነውር የሆነ ተግባር እንደሆነ ትናገራለች። በመሆኑም የተቸገረው ሰው በሁለት እግሩ እንዲቆምና ኑሮውን፣ ቤተሰቡን መምራት እንዲችል ማድረግ በገዳ ስርዓት ቡሳ ጎኖፋ እንደሚበረታታ አመልክታ፤ ማህበረሰባዊ ግዴታም ተደርጎ እንደሚቆጠርም ትናገራለች።

ከዚህ መነሻ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የገዳ አስተዳደር አንድ አካል የሆነውን የቡሳ ጎኖፋ እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችን በአንድ ላይ በማቀናጀት አንድ ተቋም መመስረቱን የምትናገረው ምክትል ኃላፊዋ፤ ከዋናው የቡሳ ጎኖፋ በተጨማሪ የባህላዊ ፍርድ ቤት የሆነውንና ‹‹ጋቸነ ሲርና›› የሚባለውን፤ ሰላምና ደህንነት የሚጠብቁ ባህላዊ አደረጃጀቶችን እንዲሁም በግለሰቦች ይሁን በቡድኖች መካከል ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት የጋራ ሀቅን ለመፈለግ የሚያስችሉ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቶችን ያካተተውን፤ በሁለተኝነት ደግሞ ጠንካራ ሰላምና ደህንነት እንዲፈጠር የሚያስችለውን አደረጃጀት እንዲሁም በገዳ ስርዓት ውስጥ ተጃጅለ ለሙማ (የዜግነት አገልግሎት) የሚል ስያሜ ያለውን ባህላዊ እሴት በአንድነት በማቀናጀት ለማህበረሰቡ ምቹ በሆነ መንገድ አገልግሎት ለመስጠት ወደ ተግባር መግባቱን አብራርታለች።

ስርዓቱ በመንግስት የተፈጠረ ሳይሆን የማህበረሰቡ ሀብት የሆነ አገር በቀል (Indigenous Knowledge) እውቀት መሆኑን ጠቅሳ፣ ተጃጅለ ለሙማ በሚባለው ባህላዊ ስርዓት አንድ ነዋሪ የማህበረሰቡ አካል በመሆኑ ብቻ በዜግነቱ የሚጣልበት ማህበራዊ ኃላፊነትና ግዴታ እንደሆነ ትገልፃለች። አንድ ሰው የኦሮሞ ብሄር አባል ሲሆን የአካባቢውን ተፈጥሮ መጠበቅ (መንከባከብ)፣ የተጎዱትን ማገዝ፣ አረጋውያንን መርዳት እና ልዩ ልዩ ኃላፊነቶችን መወጣት ከጥንትም የነበረና እንደ ግዴታ የሚቆጠር መሆኑንም ትናገራለች።

እንደ ኮሙኒኬሽን ምክትል ኃላፊዋ ገለፃ፤ በአንድ ድርጅት ውስጥ የተካተቱት ቡሳ ጎኖፋን ጨምሮ ሌሎች ሶስት እሴቶች በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ አነሳሽነት ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ባህላዊ እሴቶች ናቸው። ድርጅቱም ልማትና ሰላምን እንደሚያረጋግጥ ታምኖበት ሁሉን አቀፍ የሆነ እድገት እንደሚያመጣ ታስቦ የተደራጀ ነው።

ጎረቤት ከጎረቤት ተቀያይሞና ግጭት ፈጥሮ በቅራኔ ውስጥ እንዳይቆይ ችግሩን ባህላዊ ፍርድ ቤት መፍታትና ማስታረቅ፤ ሰላምና ደህንነትን ለመጠበቅ ደግሞ በጋቸነ ሲርና፤ አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን እና ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙ ተቋማትን ለማልማት፣ ችግኝ ለመትከል፣ የአፈርና የውሀ ጥበቃ ስራ፣ የበጎ ፍቃደኝነት ስራ ለማከናወን ደግሞ በተጃጅለ ለሙማ አደረጃጀቶች በማከናወን፣ ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት ተጎጂዎችን ለማቋቋም፣ ድርቅ ቢከሰት ተጎጂዎችን ለማገዝ በዘላቂነት ችግራቸውን እንዲፈቱ ለማስቻል የቡሳ ጎኖፋ እሴትን ተግባራዊ የሚደረግበት ወጥ ተቋም ተመስርቶ አሁን በክልሉ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ቡሳ ጎኖፋና መሰል የኦሮሞ ማህበረሰብ እሴቶች በሉላዊነት (Globalization) ተፅእኖ ስር በመግባታቸው ባህሉ ቀስ በቀስ የመጥፋትና እሴቶቹም በዘመናዊነት ተፅእኖ ውስጥ የመውደቅ ችግር እያጋጠማቸው መሆኑን የምታነሳው ምክትል ኃላፊዋ፤ በተለይ ከ1960ዎቹ ትውልድ ወደዚህ ያለው ማህበረሰብ በፖለቲካና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ውጪ የማማተርና የራሱን እሴቶች የመዘንጋት እክል እንዳጋጠመው ትናገራለች።

> ይህን መሰል የመተጋገዝና የመተባበር እሴት በኦሮሞ ማህበረሰብ የገዳ ስርዓት ከጥንት ጀምሮ የነበረና አሁንም ድረስ ተጠብቆ የቆየ ነው። በዚህ ምክንያት የተፈጥሮም ይሁን የሰው ሰራሽ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት የማህበረሰቡ አባላት ከሀብት ንብረታቸው እንዳይጎሉ፤ ስነ ልቦናቸው እንዳይጎዳና ተስፋ እንዳይቆርጡ ከለላ የሚሆን ባህላዊ እሴት ነው።

ወይዘሮ ኤልዳና እንዳብራራችው፤ በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች አገር በቀል እውቀቶች እየተዘነጉና የሚሰጡት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ችላ እየተባለ ዜጎች የሚገባቸውን ሁሉን አቀፍ ልማት ሳያገኙ ቀርተዋል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን (በተለይ ፖለቲካዊ ለውጥ ከተደረገበት 2010 እና ከዚያ ቀጥሎ ባሉት ዓመታት) ባህላዊ እሴቶቹ ወይም አገር በቀል እውቀቶቹ ዳግም ማህበረሰቡን የሚያገለግሉበትና ችግር መፍቻ ቁልፍ መሳሪያ የሚሆኑበት መንገድ ተቀይሷል፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የምትከተለው ዘመናዊ የመንግስት አስተዳደር አሊያም የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ነው፤ ይሁንና ቡሳ ጎኖፋን የመሰሉ አገር በቀል እውቀቶች ቀድሞውንም የነበሩ በተለይ የኦሮሞ ማህበረሰብ እሴቶቹን በእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ በማካተት ተግባራዊ ሊያደርጋቸው ፍላጎት ያለው ከመሆኑ አንፃር ከዘመናዊው የአስተዳደር እሳቤ ጋር ማዋሃድ አስፈልጓል። ፈጣን እና ሁሉን አቀፍ ለውጥ ለማምጣት በዚህ እሳቤ መሄድ ተመራጭ መሆኑን የክልሉ መንግስት አምኖበት ወደ ተግባር እንዲገባ አርጓል።

‹‹በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ከዚህ ቀደም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የሚባል ተቋም ነበር›› የምትለው ምክትል ኃላፊዋ፤ ይህ ተቋም እርዳታን ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች በመቀበል የማከፋፈል ስራ ይሰራ አንደነበር ትገልፃለች። አሁን ግን በራስ አቅም ችግሮችን መፍታት እና እርስ በእርስ በባህላዊ እሴቶቹ አማካኝነት መደጋገፍ እሳቤን ለማምጣት እየተሰራ መሆኑን ትጠቁማለች።

በእርዳታ እና ድጋፍ የማህበረሰቡን ችግር ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ እንደማይቻልም ገልጻ፣ ማህበረሰቡ ችግሮቹን በራሱ አቅም ባህላዊ እሴቶቹን ተጠቅሞ እንዲፈታ ቡሳ ጎኖፋን በመንግስት እውቅናና ድጋፍ ማቋቋም ማስፈለጉን አስታውቃለች። በዚህም ማህበረሰቡ በራሱ አቅም ችግሮቹን የሚፈታበት አደረጃጀት እንዲኖር መደረጉን አመልክታለች።

እንደ ኮሙኒኬሽንና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ምክትል ኃላፊዋ ማብራሪያ፤ በቡሳ ጎኖፋ አደረጃጀት አዲሱ ትውልድ ቀደም ያሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እሴቶቹን እንዲሁም ስርዓቶችን እንዲያውቅ እየተሰራ ነው። በእሴቶቹ ላይ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር በዚህ ስርዓት ወስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ ጎረቤቱን፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ እንዲደግፍ ለማድረግ እየተሰራ ነው።

በዚህም በኦሮሚያ ክልል በእያንዳንዱ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ 10 በሚደርሱ ትምህርት ቤቶች የቡሳ ጎኖፋ ክበብ እንዲቋቋም ተደርጓል። እስካሁን ድረስም በቡሳ ጎኖፋ አደረጃጀት ውስጥ ለመሳተፍ ፍቃደኛ በመሆን አባል የሆኑ 25 ሚሊዮን የሚደርሱ የማህበረሰቡ አባላት አሉ። በቅርቡ ዝናብ አጠር በሆኑ የክልሉ አካባቢዎች እነዚህን አባላት በማሰባሰብ ለተጎጂ ወገኖች የድንገተኛ አደጋ መከላከል ድጋፍ፣ በዘላቂነት ለማቋቋም መሰረት መጣል፣ የአደጋ ቅነሳ ስልት በመንደፍ የአነስተኛ መስኖ፣ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራና ሌሎችንም መሰል ችግሮቹን ሊፈቱ በሚችሉ ተግባራት ላይ ውጤታማ ስራዎች ተከናውነዋል። ከዚህ በተጨማሪ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ይሁንታ የተመሰረተው የቡሳ ጎኖፋ ድርጅት በክልሉ እስከ ሰባት ሚሊዮን ለሚደርሱ ተማሪዎች ምገባ እያደረገም ይገኛል።

በቡሳ ጎኖፋ ውስጥ ኢትዮጵያዊ የሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው መሳተፍ ይችላል የምትለው ምክትል ኃላፊዋ፤ ይህ ባህላዊ እሴት ብሄር፣ ቋንቋ ሳይለይ ሁሉንም ያለ ልዩነት የሚቀበል መሆኑን ትገልፃለች። በሰብዓዊነት የሚያምንና የአገር በቀል እውቀት የሆነውን የቡሳ ጎኖፋን ራዕይ የሚጋራ የሰው ልጅ በበጎ ምግባሩ ላይ ተሳታፊ የመሆንና የአደረጃጀቱ አባል የመሆን መብት እንዳለው አመልክታለች።

ቡሳ ጎኖፋ የኦሮሚያ ክልል ውስጥ ብቻ ያለውን ችግር አስወግዶ የሚቀመጥ አለመሆኑን ተናግራለች፤ ከክልሉ ውጪ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ተመሳሳይ ችግር ቢፈጠር ድጋፍ ለማድረግና ስርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰራ መሆኑንም ገልፃለች። ለዚህ ማሳያ ከዚህ ቀደም በኮንሶ እንዲሁም ጎፋ በመሳሰሉ አካባቢዎች ባጋጠሙ ችግሮች ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ፈጥኖ በመድረስ እና የመረዳዳት ግዴታውን መወጣቱን ተናግራለች። በቀጣይም በክልል ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ፤ በዚህም ብቻ ሳይገደብ በመላው ዓለም ለሰው ልጆች መድረስና ሰብዓዊ ድጋፍን የማድረግ ራዕይው እንዳለውም አብራርታለች።

# ስፖርት





# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በቺካጎ ማራቶን ለድል ታጭተዋል

**ብርሃን ፈይሳ**

ከዓለም ዋና ዋና ከሚባሉት ስድስቱ የማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው የቺካጎ ማራቶን ከነገ በስቲያ ይካሄዳል፡፡ መነሻውን በግራንት ፓርክ በማድረግ በታላላቆቹ የቺካጎ ከተማ ጎዳናዎች ላይ የሚካሄደው ውድድር ዘንድሮ ለ46ኛ ጊዜ ሲካሄድ 50 ሺ የሚሆኑ ተሳታፊዎች እንደሚሮጡ ታውቋል፡፡ ከሕዝባዊው ሩጫ ባለፈ አጓጊ የሆነው የታዋቂ አትሌቶች ፍልሚያም የኢትዮጵያ እና ኬንያ የማራቶን ከዋክብት አትሌቶችን ያገናኛል፡፡

ፈጣን ሰዓት ከሚመዘገብባቸው የማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ በሆነው የቺካጎ ማራቶን ባለፈው ዓመት የዓለም ክብረወሰን መሰበሩ የሚታወስ ሲሆን፣ ከወራት በፊት በመኪና አደጋ ሕይወቱ ያለፈው ኬንያዊው ኬልቪን ኪፕቱም የሰው ልጅ ማራቶንን ከ2 ሰዓት በታች የማጠናቀቅ ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋገጠው በዚህ መድረክ ነበር፡፡ የዘንድሮው ውድድርም ለዚህ ድንቅ አትሌት መታሰቢያ ሆኖ ይካሄዳል፡፡ በውድድሩ እንደሚካፈሉ ያረጋገጡ አትሌቶችን ብቃትና ያላቸውን ሰዓት ተከትሎም ከባድና ፉክክር እንደሚኖር ከወዲሁ ተገምቷል።፡

የአትሌቲክስ ቤተሰቡ ዓይን በጎረቤታሞቹ ሃገራት ኮከብ አትሌቶች ላይ ያተኮረ ቢሆንም፤ በርቀቱ ልምድ ያላቸውና በበርካታ የጎዳና ላይ ሩጫዎች ድልን በመቀዳጀት ብቃታቸውን




አትሌት ብርሃኑ ለገሰ፤

ያስመሰከሩት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ ብርሃኑ ለገሰ፣ ዳዊት ወልዴ፣ አምደወርቅ ዋለልኝ፣ ጀማል ይመር እና ሁሰዲን ሞሃመድ በወንዶች መካከል በሚካሄደው ውድድር የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው፡፡ ባለው ፈጣን ሰዓት ቀዳሚ ሆኖ የሚመራው አትሌት ብርሃኑ በበርሊን ማራቶን ያስመዘገበው 2:02:48 ሰዓት በቺካጎው ፉክክር ፈጣኑ አትሌት አድርጎታል። የሁለት ጊዜ የቶኪዮ ማራቶን ቻምፒዮኑ ይህ የቺካጎ ማራቶን ተሳትፎው ሁለተኛው ነው፡፡ በዚህ የፈረንጆች ዓመት የሮተርዳም ማራቶን ተሳትፎው ሶስተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀ ቢሆንም በቺካጎ ውጤታማ ለመሆን በሚያስችለው ብቃት ላይ እንደሚገኝ ተጠቁሟል፡፡

ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ዳዊት ወልዴ ለአሸናፊነት በሚደረገው ጠንካራ ፉክክር ለአሸናፊነት ትልቅ ግምት የተሰጠው ኮከብ




አትሌት ሱቱሜ ከበደ፤

ነው፡፡ ዳዊት ምንም እንኳን በቫሌንሲያ ማራቶን ያስመዘገበው 2:03:48 የሆነ የግሉ ፈጣን ሰዓት ከብርሃኑ በአንድ ደቂቃ የዘገየ ቢሆንም ቀላል ግምት የሚሰጠው አትሌት አይደለም፡፡ በኬንያ በኩል ከሚሳተፉ አትሌቶች መካከል የአሸናፊነት ግምት ያገኘው እአአ በ2019 የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የማራቶን የነሐስ ሜዳሊያ አሸናፊው አሞስ ኪፕሩቶ ይገኝበታል። አትሌቱ የ2022 የለንደን ማራቶን አሸናፊ መሆኑ ደግሞ በዚህ ውድድርም ለውጤት እንዲጠበቅ አድርጎታል። ሌላኛው ኬንያዊ አትሌት ቪንሰንት ጌቲችም ከተጠባቂዎቹ አትሌቶች ተርታ የተቀመጠ ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት የበርሊን ማራቶንን ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቁ ይታወሳል፡፡

በሴቶች መካከል በሚካሄደው ውድድር ፈታኝ ፉክክር እንደሚኖር ከወዲሁ መገመት ይቻላል። በተለይም በቺካጎ ማራቶን የሁለት ጊዜ አሸናፊ (2021 እና 2022) መሆን የቻለችው ኬንያዊቷ ሩት ቺፕንጌቲች ፊቷን ዳግም ወደ ውድድሩ መመለሷ ተጠባቂ እንድትሆን አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ከቺካጎ ማራቶን በሚስተካከለው የቶኪዮ ማራቶን በቅርቡ አሸናፊ የነበረችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ሱቱሜ ከበደ በቀላሉ ልትበገር የማትችልና ለኬንያዊቷ አትሌትም አስፈሪ ተፎካካሪ እንደምትሆን ይጠበቃል። ውድድሩን ይበልጥ ተጠባቂ ያደረገው ደግሞ ከሱቱሜ ባለፈ እንደ ደጊቱ አዝመራው፣ አሼቴ በከሪ፣ ሕይወት ገብረኪዳን እና ቡዜ ድሪባን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን የማራቶን ኮከቦች የውድድሩ ተሳታፊ መሆናቸው ነው፡፡

በቶኪዮ ማራቶን 2:15:55 የሮጠችው ሱቱሜ በዓመቱ ከተመዘገቡ የርቀቱ ፈጣን ሰዓቶች ቀዳሚውን ስትይዝ፤ በሂውስተን ግማሽ ማራቶን ውድድርም በተመሳሳይ በአሜሪካ ከተካሄዱ ውድድሮች በርቀቱ እጅግ ፈጣኑን ሰዓት የግሏ ማድረግ ችላለች፡፡ ይህም የአትሌቷን ወቅታዊ ብቃት የሚጠቁም ሲሆን፤ በቺካጎ አሸናፊ በመሆን ታጠናቅቃለች ተብሎ ይጠበቃል። ጠንካራ የአሸናፊነት ፉክክር እንደሚያደርጉ የሚጠበቁት ሱቱሜ እና ቺፕጌቲች እርስ በእርስ ሲገናኙ ይህ የመጀመሪያቸው አይደለም፡፡ እአአ በ2019ኙ የኒውዮርክ ማራቶን እንዲሁም በ2021 ደግሞ በለንደን ማራቶን ተፎካክረዋል፡፡ ከነገ በስቲያ የሚካሄደው የቺካጎ ማራቶንም ለሁለቱ አትሌቶች የአሸናፊዎች አሸናፊ ፉክክር ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡


## የጨረታ ማስታወቂያ

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ለቆሬ ዋር ኮሌጅ እና ድሬዳዋ ፌዴራል ፖሊስ ሆስፒታል ፕሮጀክቶች ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ዝርዝራቸው ከጨረታ ሰነዱ ጋር በተያያዘ የስራ ዝርዝር (Specification) መሰረት Fire Pump and Domestic Pump አቅርቦትና ገጠማ እንዲሁም የ Sanitary fixture አቅርቦት ግዥ ለመፈፀም ተጫራቾችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የስራ ዝርዝር | የጨረታ ቁጥር | የጨረታ መዝጊያ ቀን | የጨረታ መክፈቻ ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Supply & Fix:-<br>1.1 Fire Pump<br>1.2 Domestic Pump | DCE/ SF/100/2024 | 15/02/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 | 15/02/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡45 |
| 2 | Sanitary Fixture | DCE/ SM/101/2024 | 15/02/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡45 | 15/02/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 5፡00 |

**ስለሆነም፡-**

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩ፣ ህጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ እና የታደሰ ታክስ ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ለእያንዳንዱ ጨረታ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በባንክ በተረጋገጠ CPO ወይም ከታወቀ ባንክ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (unconditional Bank Guarantee) ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ በጨረታ ሠነዱ በተጠቀሰው ብዛት እና ስፔስፊኬሽን መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) በመክፈል ዘወትር በስራ ሰዓት ቃሊቲ ቶታል ስታዲየም ጀርባ ወይም ኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉ ት/ቤት አጠገብ በሚገኘው የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ዋናው መስሪያ ቤት የግዥ እና አቅርቦት አስተዳደር መምሪያ መግዛት ይችላሉ፡፡
5. አንድ ተጫራች መወዳደር የሚችለው በአንድ ዓይነት ሞዴል /ብራንድ/ብቻ ነው፤ በአማራጭ የቀረበ ዋጋ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
6. ኢንተርፕራይዙ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የቀጥታ ስልክ ቁጥር ቁጥር፡- 0114-40-34-34/33 ማዞሪያ 0114-42-22-70/71/72 www.dce et.com / Email:-info@dce-et.com ቃሊቲ ቶታል ስታዲየም ጀርባ ወይም ኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉ ት/ቤት አጠገብ

**የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ**

## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

የደሴ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለ2017 ዓ.ም በጀት አመት ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚውል ከኢትዮጵያ መድሃኒት አቅርቦት አገልግሎት (EPSS) ሳይኖር ሲቀር መድሀኒቶች፣ሰፕላይ፤ ላብራቶሪ ሪኤጀንት ለአንድ አመት የሚቆይ የህክምና መሳሪያ ጥገና፣ ለአንድ አመት ጊዜ የሚቆይ የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ለአንድ ጊዜ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፤

**ስለሆነም አግባብነት ያላቸውን ሁሉ በጨረታው እየጋበዝን፡-**

1. ተጫራቾች ለተወዳደሩበት የአቅርቦት አይነት የተዛመደ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው::
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቲን-ነምበር ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. የግዥው መጠን ከ200,000 በላይ ከሆነ የቫት ተመዝጋቢ የሆነ፡፡
5. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ ከላይ ከተራ ቁጥር ከ1-4 የተገለፁትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከጨረታው ኦሪጅናል ሰነዶች ጋር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 15 የስራ ቀናት ከሆስፒታሉ ግዥ ክፍል የማይመለስ 300 ብር በመክፈል ማግኘት ይችላሉ::
7. ተጫራቾች የጨረታ ዋስትና ከሚያቀርበው ጠቅላላ ዋጋ 2% ሲፒኦ ከኦርጅናሉ የጨረታ ጋር በማያያዝ በታሸገ ፖስታ ሙሉ ስምና አድራሻ ጽፎ ማቅረብ ይኖርበታል በተጨማሪም ኦርጅናል ሰነዱ እና ፎቶ ኮፒ ለብቻው ሙሉ አድራሻው ተጽፎ በጥንቃቄ ታሽጎ መቅረብ አለበት፡፡
8. የጨረታው ተሳታፊዎች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው በማስታወቂያ በወጣበት በመጨረሻ የስራ ቀን ከቀኑ 4፡00 ታሽጎ በእለቱ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡

9 ሆስፒታሉ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

10. ሆስፒታሉ ቫት እና ዊዝ ሆልድ (2%) ቆርጦ የሚያስቀር መሆኑን እንገልፃለን፡፡
11. ሆስፒታሉ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፤

**የደሴ አጠ/ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል**